# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል"

## ቅጽ ሁለት

ርዕስ ፡የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ (የመጣጥፎች ስብስብ)

ጸሐፊ ፤አማኑኤል እንዳለ

Gmail :- amanuelendale223@gmail.com

Facebook :- www.facebook.com/amani.love.902

Telegram :- @SDG1517

Phone +251949241635

© 2013

መብቱ በሕግ የጠበቀ ነው፤ ያለ ጸሐፊው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ ከሥራው የተወሰነውን ክፍል ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው።

## *ምስጋና*

ከሁሉ አስቀድሜ አለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱስና ነውር አልባ እሆን ዘንድ ለመረጠኝ ከእኔ በሆነ ምንም ምክንያት ላልተደገፈ ለታላቁ ጌታ እግዚአብሔር አብ ክብርና ምስጋና ይሁን። እንዲሁም ደግሞ በበደሌና የሥጋዬን ኀጢአታዊ ባሕርይ ባለመገረዝ ሙታን ሳለሁ ደዌዬን ለተቀበለ በእኔ ላይ ሊያርፍ የተገባውን ቅጣት ተሸክሞ ከራሱ ጋር ላስታረቀኝ ደግሞም ከአባቱ ጋር ዘላለማዊ እርቅን ላወረደልኝ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ይሁንለት። የመስቀሉን እውነት በልቤ ላበራ ድንጋዩን ልቤን በሥጋ ልብ ለቀየረ ቃሉን በቅዱሳት ባሪያዎቹ በኩል ለሰጠኝ ደግሞም በቃሉ መኖርን እና መደሰትን ሁልጊዜ ለሚያድለኝ ለእርሱ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር እና ምስጋና ይሁንለት። አሜን።

በመቀጠል በዚህ የእምነት ዕቃቤ አገልግሎት እንድበረታ በተለያየ አጋጣሚ የደገፉኝ ዐርዐያ የሆኑኝ ወንድም ዘላለም መንግስቱ፣ ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ እና በሶዶ መጥመቃዊት ቤተ ክርስቲኣን መጋቢ ተስፋጺዮን አለማየሁ ጌታ እናንተን በእኔ ዘመን ሰላኖረ እግዚአብሔርን ስለመግቦቱ አመሰግናለሁ። ወንድም አማረ ታቦር (Amex) በሩቅ ሆነህ ነገር ግ በአካል የማውቅህ ያክል ወንድምነትህን የማይብህ ደግ ወንድሜ ጌታን ስላንተ አመሰግናለሁ። <<Chrstianity in Chrsis>> የሚለው የሃንክ ሃንግረፍ መጽሐፍ በብዙ ጠቅሞኛል በየዕለቱ

ለማዘጋጃቸው መጣጥፎች ዋቢ አድርጌ በዋናነት ተጠቅሜዋለሁ ይህ የአንተ ምርጡ ስጦታዬ ነው አሜክስ ወንድሜ እግዚአብሔር ጸጋን ያበዛልህ ዘንድ እመኛለሁ።

የመጨረሻው ጽሁፍ ከመልቀቂ ቀደም ብዬ የእርማት ስራውን እንዲሰራ የሰጠሁት ወንድሜ አቤኔዘር ዳንኤል ከዕረፍትህ ቆርሰህ በዚህ አገልግሎት አብረኸኝ ስለደከምክ ጌታ ያክብርልኝ።

በዚህ በስም ያልዘረዘርኳችሁ አያሌ ሰዎች አላችሁ ስማችሁን ብዘረዝር እርሱ እራሱ አንድ ሌላ መጽሐፍ ይሆንብኛል ብዬ እንጂ ግልጽ ነው። ልቤ በስም ጠርጧችኋል ከምንም በላይ ደግሞ በጌት ዘንድ ታውቃችኋል በዙሪያዬ ሰላላችሁ ደጋግ ሰዎች እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

## *ከመጽሐፉ ምን እንጠብቅ?*

ከዚህ መጽሐፍ ከአንድ የስነ መለኮት ትምህርት ቤት ምሩቅ የጻፈውን አይነት ጽሁፍ አትጠብቁ ይልቅ አንድ ለእግዚአብሔር ቃል ፍቅር ያለው ወንድሞችን በጊዜው ተንሰራፍቶ ካለ ኑፋቄ የተረዳውን ነገር በማቅረብ ቅዱሳን ይታነጹ ዘንድ አድርጋችሁ ተቀበሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ጠንከር ያሉ የስነ መለኮት ቃላት ወይም ማብራሪያ ያላገኛችሁ እንደሆን የአንድ ለቅድስት ቤተ/ን የሚቀና ሰው ጽሁፍ ነውና ኣንደዚያ ተመልክታችሁ ልታናግሩኝ ትችላላችሁ። ጌታ በረዳኝ መጠን ጠንካራ ሙግቶችን በርዕስ ለማንሳት ሞክሬያለሁ ቀሪው እናንተ አንብባችሁ የምትሉኝ ነገር ቢሆንም ማለቴ ነው።

# አበርክቶት

በሐገራችን በዕቅብተ እምነት አገልግሎት በመትጋት ለሚያተጉን ወንድም ዘላለም መንግስቱ እና ወንድም ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ ይሁንልኝ።

## ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 8

“ክርስቲያን አይታመም፣ ክርስቲያን አይደኸይም።” ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 16

**“**ክርስቲያን አይታመም፣ ክርስቲያን አይደኸይም።**”** ........ 16

ክፍል ሦስት ........ 24

**"**በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ተባርክናል**"** ........ 24

ክፍል አራት ........ 34

**"**በመገረፉ ቁስል ተፈውሰችኗል**"** ........ 34

ክፍል አምስት ........ 39

**"**በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ**” 2**ቆሮ **8፥9** ........ 39

ክፍል ስድስት ........ 45

**“**በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።**”** ........ 45

ክፍል ሰባት ........ 51

**"**ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።**"** ........ 51

ክፍል ስምንት ........ 55

የቃል እምነት አስተምህሮ በእምነት አባቶች ሕይወት ሲዳኝ ........ 55

ክፍል ዘጠኝ ........ 61

ማጠቃለያ፡**-** ........ 61

ስለ በሽታ እና ድኽነት ምን ልናውቅ ይገባል**?** ........ 61

ዋቢ መጽሐፍት ........ 68

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

**ክፍል አንድ**

መግቢያ፡-

***"ክርስቲያን አይታመም፣ ክርስቲያን አይደኸይም፡፡"***

በባለፈው ቅጽ **(**ቅጽ **1)** የቃል እምነት ኑፋቄ ዳሰሳዬ ላይ ***"****ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል፡፡****"*** የሚለውን ስሁት አስተምህሮ በአምስት ክፍሎች ከፋፍዬ፤ እንዲሁም ማጠቃለያ በመስጠት ይህንን ርዕስ **(**ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል የሚለውን**)** ቋጭቼ ነበር። በዚህ ቅጽ **(**ቅጽ **2)** ደግሞ በእነዚሁ መናፍቆች የሚነሱትን ሌላኛውን ትምህርት የምንዳስስ ሲሆን፤ አካሄዳችን ልክ በመጀመሪያው ቅጽ ላይ እንዳደረኩት በመጀመሪያ የአመክንዮ ዉቃሬያቸውን በራሱ የሥነ**-**አመክንዮ ሕግ በመመራት፤ ሙግታቸው ደካማ እና ሕጸጽ ያለው እንደሆነ በመመልከት፤ ቀጥሎ ደግሞ የሚጠቅሷቸው ምንባባትን አውዱን በተከተለ ፍታቴ በማድረግ እውነተኛውን የቃሉን ፍቺ የምንመለከት ይሆናል። መልካም ምንባብ።

የብልጽግና **"**ወንጌል**"** የሚለው መጠሪያው**(**ርዕሱ**)** ራሱ በግልጽ ሊያስተምረን የሚችልው ግልጽ መልዕክት አለው። በዚህ አስተምህሮ መሠረት አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ በኋላ እግዚአብሔር ያንን ሰው በምድራዊ ነገሮች የበለጸገ እና ሙሉ ጤነኛ ይሆን ዘንድ አድርጓል በማለት ያስተምራሉ። ይህ አስተምህሮ የሚለው እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ያኖረው በደህንነት ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ፡**-** በድህነት ላይ፣ ሥጋችን ጤናማ ይሆን ዘንድ፣ ኑሯችንም የበለጸገ እንዲሆን ነው በማለት ነው። መቼም ነገርን ከምንጩ መቅዳት ጥሩ ነውና፤ በቀጥታ የዚህ አስትምህሮ ቀንደኛ አቀንቃኝ የሆነውን ኬኔት ኮፐላንድን ዋቢ አድርገን እንመልከት እስቲ፡**-**

***"You have a covenant with Almighty God, and one of your covenant rights is the right to a healthy body"*** *ኬኔት ኮፐላንድ አሁንም ይቀጥልና* ***"The first***

***step to spiritual maturity is to ralize your position before God. You are a child of God and a joint-heir with Jesus. Consequently, you are entitled to all the rights and privileges in the kingdom of God, and one of these right is health and healing. You will never fully realize or understand healing untill you know beyond any doubt that...God wants you healed....Wheater or not you accept that and purpose to walk in the reality of the truth is your own decision to make."***

ቤኒ-ሂን ይህንን የኮፐላንድን ንግግር ቁርጥ ባለ ቋንቋ ሲናገር፡-

***"The bible declares that the work was done 2,000 years ago. God is not going to heal you know-He healed you, 2,000 years ago. All you have to do today is recieve your healing by faith."***

ከላይ ያለውን ንግግር በአንድ ወጥ አረፍተ ነገር ብናስቀምጥ ኮፐላንድ እና ቤኒ-ሂን ሊሉን የፈለጉን፡-

*"እግዚአብሔር የዛሬ **2000** ዓመት ገደማ ከክርስቶስ ጋር ቃል ገብቷል፤ ፈውስ እና ብልጽግና የዚህ ቃል-ኪዳን አካል ነውና አሁን ከእኛ የሚጠበቀው ፈውሳችንን በእምነት መቀበል ነው"* የሚል ይሆናል ማለት ነው።

በብልጽግና አስተምህሮ አንድ ሰው ለመዳን ምንም ታደርግ ዘንድ አይገባህም በክርስቶስ በማመን ብቻ ትድናለህ እንደሚባለው ሁሉ፤ ለፈውስም ምንም ማድረግ አይጠበቅብህም *"ስታምን ባለጸጋ እና ጤናማ ትሆናለህ"* በማለት ይሰብካሉ፤ ደግሞም ያስተምራሉ።

በአንድ አጋጣሚ አቶ ብስራት ብዙአየሁ (ዷፒ) ከሃገር ወጥቶ ሲመለስ የዚህ አስተምህሮ ተከታቶች ሆ ብለው በመውጣት አቀባበል አድርገውለት ነበር። እዚያ አቀባበል ላይ ብዙ መናፍስቶች *(ያው "መንፈስ ነን" ብለውን የለ፤ መንፈሶችን በብዙ ቁጥር መናፍስት ነው የምንለው)* በመገኘት የእንኳን ደህና

መጣህልን ንግግር ሲያደርጉ፣ በመሀላቸው አንድ ወንድም ክርስቲያን አይታመም የሚል አቋም ያለው በመካከላቸው ተገኝቶ ነበር። ይህ ወንድም ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ገና ንግግር ማድረግ ከመጀመሩ ***"ከሰሞኑን ጉንፋን ነገር እያመመኝ ነበር"*** በማለት ሳለ ገና ንግግሩን ሳይጨርስ በስፍራው ያሉ ሰዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ***"እረ አልታመምክም ካደው!"*** በማለት ዋሽተው ወደ ውሸታቸው ጋብዘውት ነበር።

ይህን ዓይነት የአዕምሮ በሽተኛ የሚያደርግ ትምህርት የተቀበሉት ደግሞ ***Jerry Savelle*** ከተባለች የዚሁ ኑፋቄ አስተማሪ ነው። እርሷ በአንድ አጋጣሚ የጉንፋን ሕመም ምልክቶችን በራሷ ላይ ስታስተውል ሰላደረገችው ነገር ስታስተምር እንዲህ ብላ ነበር፡-

***"When the Devil tries to put a symptom of sickness or disease on my body. I absolutly refuse to accept it. A short time ago he tried to put symptoms of the flu on me. My nose and eyes and nose started to run. I began to sneeze and ache all over. I havent had the flu 1969, and i am not going to have now. I am redeemed from the flu! Immediatly i began to confess God's word that I am healed by the stripes of Jesus. I rebuked Satan and refused his lying symptoms. I wasnt trying to get something i dont have; i was keeping something i already have. I am healed"***

ስለዚህ የዚህ ኑፋቄ ሰለባዎች ታመው ***"አልታመምኩም"*** የሚሉ ዋሾዎች(ውሸታሞች) በኪሳቸው ገንዘብ እንደሌለ እያወቁ ይህንን ክደው ***"አለኝ"*** የሚሉ ሞኞች ናቸው። ከላይ ያወራሁትን ሁሉ በሙግት መልክ ላቅርብና እሱን አይተን እንጨርሳለን።

**i)** እግዚአብሔር በክርስቶስ የሆኑትን በሽታ እና ድህነት እንዳይነካቸው አዟል።

**ii)** አቶ አበበ በክርስቶስ ነው።

**iii)** ስለዚህ አቶ አበበ በፍጹም አይታመም፤ ደግሞም በፍጹም ደሃ ሊሆን አይችልም።

ከዚህ ቀደም ሙግት ሁል ጊዜም ድምዳሜ ጋር ከመሄዳቸው በፊት ለድምዳሜው ግብዓት ይሆን ዘንድ የቀረበውን **Premises** ወይም መነሻ ነጥቦችን ተመልክተን ደካማ ሙግት **(Weak argument)** ወይም ጠንካራ ሙግት **(Sound argument)** ልንል እንችላለን።

ከላይ ኮፕላንድ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል-ኪዳን በተመለከተ ስለ ብልጽግና እና ጤና ነው በማለቱ ይህንን የመጀመሪያውን መንደርደሪያ ነጥብ አንስቷል። እስቲ ይህንን ክፍል እንመልከት። ከዚያ ደግሞ ይህ ከማንም ቀድሞ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ከሐዋርያቱ ምድራዊ ሕይወት ጋር በማነጻጸር እንመለከታለን።

*<u>ዘፍጥረት **12** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*² "ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ ደግሞም እባርክሃለሁ፤*

*ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎች በረከት ትሆናለህ።*

*³ የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህን እረግማለሁ፤*

*በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ።"*

*<u>ዘፍጥረት **15** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*² አብራምም፣ "እግዚአብሔር **(ያህዌ)** አምላክ ሆይ፤ ያለ ልጅ የቀረሁ ስለ ሆንሁ፣*

*የቤቴ ወራሽ የደማስቆ ሰው ኤሊዔዘር ነው፤ ታዲያ ምን ትሰጠኛለህ?" አለው።*

*³ "አንተ ልጆች ስላልሰጠኸኝ፣ ከቤቴ አገልጋይ አንዱ ወራሼ መሆኑ አይቀርም።"*

*⁴ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር **(ያህዌ)** ቃል እንዲህ ሲል መጣለት፤*

*"ይህ ሰው ወራሽህ አይሆንም፤ ነገር ግን ከአብራክህ የሚከፈል ልጅ ወራሽህ ይሆናል።"*

*⁵ ወደ ውጪም አውጥቶ፣ "ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ እስቲ መቍጠር ከቻልህ፣*

*ከዋክብቱን ቍጠራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል” አለው።*

*6 አብራም እግዚአብሔርን (ያህዌ) አመነ፤ እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት።*

*__ዘፍጥረት 17 (አዲሱ መ.ት)__*

*2 በእኔና በአንተ መካከል የተመሠረተውን ኪዳን አጸናለሁ፤ ዘርህንም እጅግ አበዛለሁ።”*

*3 አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለው፤*

*4 “እነሆ፤ የምገባልህ ኪዳን ይህ ነው፤ የብዙ ሕዝቦች አባት ትሆናለህ።*

*5 ከእንግዲህ ወዲያ ስምህ አብራም መባሉ ቀርቶ አብርሃም ይሆናል፤ የብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌሃለሁና።*

*6 ዘርህን እጅግ አበዛለሁ፤ ብዙ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ።*

*7 በእኔና በአንተ፣ ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር ከትውልድ እስከ ትውልድ የዘላለም ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤*

*በዚህም የአንተና ከአንተም በኋላ የዘርህ አምላክ (ኤሎሂም) እሆናለሁ።*

እንግዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ሰላደረገው ኪዳን የምናገኘው ምንባብ ከላይ ባሉት ሲሆን ይህንን ምንባብ በሁለት መልኩ የምንመለከት ይሆናል።

**አንደኛው፡-** እነዚህ ምንባባትን ትርጉም ማለትም እግዚአብሔር ለአብርሃም እየገባለት ሰላለው ኪዳን አብርሃም እንዴት እንደተረዳው እና ከእርሱ በኋላ የእርሱ ዘር የሆኑት አይሁድች በዚህ ምንባብ ላይ ያላቸውን መረዳት መመልከት ሲሆን።

**ሁለተኛው፡-** ደግሞ እነዚህን ምንባባት ቅዱስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትርጓሜ በመስጠት አማኞች ወይም ቤተ-ክርስቲያን እና አብርሃምን አያይዞ ምንባቡን በሚፈታበት መንገድ በማየት ይህንን ምንባብ የምንረዳ ይሆናል።

አብርሃም ሆነ ይህ መልዕክት የተጻፈላቸው አይሁዳዊያን የዚህ ምንባብ ቀዳማይ ተደራሲያን ናቸውና የእነርሱ መረዳት ብናውቅ ክፍሉን በትክክል የምንተረጉም ይሆናል። ለመሆኑ አብርሃም ይህንን ክፍለ ምንባብ የሚረዳው እንዴት ነው**?**

አብርሃም በመጀመሪያ ስሙ *አብራም* ነበር። ከከለዳዊያን ቤተሰብ ሲሆን ጣዖትን አምላኪ ነበር፤ በዚህ ሁኔታ እያለ እግዚአብሔር አንድን ሰው በሉዐላዊ ምርጫው በመምረጥ የእርሱን ዘር የራሱ ሕዝብ አድርጎ ይወስድ ዘንድ ፈቀደ። ይህም ሰው ኋላ ላይ የብዙዎች አባት ትሆናለህ የተባለለት *አብራም* ሲወጣ *አብርሃም* የተባለው ሰው ነው።

ይህንንም ሲያመለክት ***"****ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለው እና ስምህን ገናና አደርጋለሁ****"*** በማለት እግዚአብሔር በዚህ ሰው በኩል ስለሚመጣው ሕዝብ ያውጅ ጀምሯል። እግዚአብሔርም አብራምን ***"****ከወገንህ ቤት እኔ ወደማሳይህ ስፍራ ውጣ****"*** በማለት ካዘዘው በኋላ አብራም ገናና እንደሚሆን እግዚአብሔር ተናገረለት። ከምንም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር አብርሃምን እና በእርሱ በኩል ሊመጣ ሰላለው ዘር ሲናገር ልክ እንደሌላው ያለ አይነት ሕዝብ ሳይሆን የእግዚአብሔር ህዝብ መሆኑን፤ በዚህም ምክንያት ነው አብራምን ወይም የአብርሃምን ዘር የሚራገም ይህ ጠላትነት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ የተናገረው።

ይህ ቃል**-**ኪዳን እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ኪዳን ነው። ይህ ኪዳን ግልጽ እና ምድራዊ በረከትን የሚናገር ሲሆን ተፈጻሚነቱ እንደ ተቀዳማይ ደራሲያን አተያይ ከሆነ የአብርሃም ዘር የሆኑት እነርሱ ታላቅ እና ገናና ሕዝብ ሆነው እግዚአብሔር ተስፋ በገባላቸው መሠረት በከነዓን መኖር ፍጻሜው ነው። ይህም አይሁዳዊያን ወይም በአዲስ ኪዳን በአብዛኛው ጊዜ ፈሪሳዊያን ራሳቸውን የተለየ ሕዝብ አድርገው የሚመለከቱበት ምክንያት ነው። ይህ የተስፋ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በምናነብበት ጊዜ የምንረዳው ሲሆን፤ ፍጻሜው በመጨረሻም ኢያሱ ሕዝቡን ይዞ ከነዓን ሲገባ ሆኗል።

<u>*ኢያሱ* ***23*** ***(****አዲሱ መ****.****ት****)***</u>

*14 “እነሆ፤ አሁን የምድርን ሁሉ መንገድ ልሄድ ነው፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር*

*ከሰጣችሁ መልካም ተስፋ ሁሉ አንዷቱን እንኳ እንዳላስቀረባችሁ፣*

*በፍጹም ልባችሁ በፍጹም ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ፤ አንዱም ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሞአል።*

*15 ነገር ግን አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ መልካሙ ተስፋ በሙሉ እንደ ተፈጸመ ሁሉ፣*

*እንደዚሁም አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከመልካሚቱ ምድር እስኪያጠፋችሁ*

*ድረስ ክፉውን ነገር ያመጣባችኋል።*

*16 አምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ኪዳን ብታፈርሱ፣ ሄዳችሁም ሌሎችን*

*አማልክት ብታገለግሉና ብትሰግዱላቸው የእግዚአብሔር ቍጣ በላያችሁ ይነዳል፤*

*ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ ምድር በፍጥነት ትጠፋላችሁ።”*

ሕዝቡም ገናና እና በአህዛብ ዘንድ የሚ**[**ፈ**]**ራ ሆኗል። በዚህም እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ መፈጸሙን ኢያሱ ይናገራል። ኢያሱ ስለዚህ ተስፋ መፈጸም ግልጽ በሆነ ቋንቋ እንዲህ ተናግሯል**:-**

*ኢያሱ **21** (አዲሱ መ.ት)*

*44 እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶቻቸው እንደ ማለላቸው*

*በዙሪያቸው ካሉት አሳረፋቸው፤ አንድም ጠላት ሊቋቋማቸው አልቻለም፤*

*እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሁሉ አሳልፎ በእጃቸው ሰጥቶአቸዋልና።*

*45 እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከሰጠው መልካም የተስፋ ቃል*

*አንዳችም አልቀረም፤ ሁሉም ተፈጽሞአል።*

መጽሐፍ ቅዱሳችንን በራሱ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ቋንቋ እንፈታ ዘንድ ግድ ነው፤ ከእኛ ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ ሳይሆን ከመጽሐፉ ወደ እኛ ሊሆን ይገባል። ትርጉሙን ከላይኛው ምንባብ የፈለግን እንደሆነ እግዚአብሔር ለአብርሃም ኪዳን ገባለት፤ ይህም ኪዳን ፍጻሜውን አግኝቷል የሚለው ነው።

ማንኛውም ሰው እነዚህን እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ምድራዊ በረከቶችን ይረዳ ዘንድ የሚገባው ነገር፡- እነዚህ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የመዳን ተስፋ፣ ልጁን ለመላክ የወሰነውን ዘር፣ እንዴት አንድን ሰው ጠርቶ ባርኮ፣ የገባለትን ተስፋ ጠብቆ ያንን ዘር ወዶ ገናና አድርጎ፣ በአህዛብ መካከል በድንቅ መርቶ ከነዓንን እንዲወርሱ እንዳደርገ በዚህም እግዚአብሔር ተስፋ የሚጣልበት ታማኝ አምላክ መሆኑን እንጂ ልክ ተስፋው እንዳልተፈጸመ አድርጎ ዛሬም ይህ ተስፋ ለእኛ በቀዳማይነት የተደረገ በማድረግ አድርጎ ማቅረብ ስህተት ነው።

ወይም ደግሞ በሌላ አማርኛ እግዚአብሔር ልጁን በመላክ እንደሚያድነን የገባውን ተስፋ ልጁ እንደመጣልን እና ይህ ትንቢት እንደተፈጸመ ሳይሆን ገና እንዳልመጣ እና እንዳልተፈጸመ አድርጎ እንደማሰብ ወይም እንደመቁጠር ይሆናል ማለት ነው፤ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ነው።

ብዙ ሕዝብ መሆኑ፣ ከገዛ ጉልበቱ የሚወጣው እንደሚወርሰው መነገሩ፤ እነዚህ ሁሉ በቀዳማይ ተደራሲው አብርሃም ሕይወት እና በአይሁዳዊያን ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም ከላይ እንዳየነው ነው።

ስለዚህ ይህ ምንባብ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ታማኝነት ነው። የእግዚአብሔር ታማኝነት ስንል እግዚአብሔር ምንም ያህል ታላቅ እና ገናና አምላክ ቢሆንም በሰው ልጆች ታሪክ በመግባት ራሱን ከሰዎች ጋር በቃል-ኪዳን የሚያስተሳስር አምላክ እንዲሁም ደግሞ ቃል ኪዳኑን ዘመኑን ጠብቆ የሚፈጽም አምላክ መሆኑምን ነው።

በቀጣይ ክፍል ደግሞ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዴት እንደተተረጎሙ የምናይ ይሆናል። ማለትም ለእኛ ለዚህ ዘመን አማኞች ክፍሉ ያለው መንፈሳዊ እንድምታ እና የጳውሎስን አተረጓጓም በማየት መርሃችንን የምንቀርጽ ይሆናል።

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ሁለት

### *"ክርስቲያን አይታመም፣ ክርስቲያን አይደኸይም።"*

በመጀመሪያው ክፍል (በክፍል 1) ላይ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ሰለገባው ቃል-ኪዳን አንስተን፣ ኪዳኑን በምን መንገድ ተፈጻሚ እንደሆነ በተለያየ መንገድ ለመመልከት ሞክረናል። በዚህ ክፍል ደግሞ (በክፍል 2) እነዚህን ምንባባት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በሚተረጉሙበት መንገድ የምንመለከት ይሆናል።

እግዚአብሔር አንዱን ሰው አብርሃም ከወገኖቹ መካከል እርሱ ወደ ሚሰጠው ምድር እንዲወጣ ካዘዘው በኋላ፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሚሰጠው በዛች ምድር የአብርሃም ዘር የሆኑ በሥጋ የእርሱ ልጆች ስለሆኑ ስለ እስራኤላዊያን ብሉይ ኪዳን ሰፊ ሐተታ ይሰጣል። እነዚህ ከአለም ሕዝብ መካከል እግዚአብሔር በመለኮታዊ ምርጫው ሕዝቡ አድርጎ የተቀበላቸው እርሱም ደግሞ አምላካቸው የሆነ አምላክ ነው። ይህ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ይለይ ዘንድ እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ የራሱን ሕጎች ሰጥቷል። እነዚህን ሕጎች ለሦስት ስንከፍል እነዚህም፦ የሞራል ሕጎች፣ የቤተ-መቅደሱ ሥርዓት እና የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ናቸው። በሥጋ የአብርሃም ልጆች የሚባሉት እነዚህ ሕዝቦች ብዙውን ጊዜ በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በኃይል በመውረድ አካል ለለበሰችው ቤተ-ክርስቲያን ታሪኳ እና ግብሯ በንፅፅሮሽ ይቀርባሉ። ለምሳሌ፦ ሐዋርያው ጴጥሮስ አማኞች ከነበሩበት የኃጢአት ባርነት ነጻ ስለመውጣታቸው ሲናገር እንዲህ ብሏል፦

***<u>1ኛ ጴጥሮስ 2፡9 (አዲሱ መ.ት)</u>***

*"እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን*

*የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣*

*የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ።"*

ይህ ምንባብ ደግሞ በሌላኛው የብሉይ ምንባብ እንዲህ ይላል፡-

*__ዘዳግም 10፥15 (አዲሱ መ.ት)__*

*“ነገር ግን እግዚአብሔር (ያህዌ) አባቶችህን ስላፈቀረ፣ ወደዳቸው፤*

*ዛሬም እንደሆነው የእነርሱ ዘር የሆናችሁትን እናንተን ከአሕዛብ ሁሉ ለይቶ መረጣችሁ።”*

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከአባቶች ጋር ሰለገባው ቃል-ኪዳን የተነሳ *ሰላፈቀረ፣ ሰለ ወደደ እና ስለመረጠ* የሚለውን ምንባብ በትይዩ በማምጣት ክርስቲያኖችም እንዲሁ ደግሞ ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የተጠሩ ልክ እስራኤላዊያን ክግብጽ ባርነት ነጻ እንደወጡ፤ እኛ አማኞች በክርስቶስ ሞት ከኀጢአት ኃይል ነጻ ወጥተናል በማለት አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ይተረጉማል። ይህንን ሃሳብ እያነሳሁ ያለሁት ለምን እንደሆነ ለማስረዳት አንድ የቤተ-ክርስቲያን አባት የተናገሩትን እዚህ ጋር ልጥቀስ፡- *"አዲስ ኪዳን በብሉይ ሥር ተሸሽጓል፤ ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጧል" (ቅዱስ ኦግስቲን)* እንዳሉት ነው።

የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ለአዲስ ኪዳን ቤተ-ክርስቲያን ትምህርት ነው። ለዚህም ነው የአዲስ ኪዳን መጽሓፍት የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በንፅፅር አቅርበው ለእግዚአብሔር ቃል ዳተኛ ለሚሆኑ ምዕመናን ማስጠንቀቂያ የሚሰጡት።

*__ዕብራውያን 3 (አዲሱ መ.ት)__*

*8 በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣ በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣ ልባችሁን አታደንድኑ።*

*9 አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፤ መረመሩኝ፤ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ ዓመት አዩ።*

*10 በዚያም ትውልድ ላይ የተቈጣሁት ለዚህ ነበር፤ እንዲህም አልሁ፤*

*‘ልባቸው ሁል ጊዜ ይስታል፤ መንገዴንም አላወቁም፤’*

*¹¹ ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤ "ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም።"*

*¹² ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያስኰበልል፣*

*ኀጢአተኛና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ።*

***1ኛ ቆሮንቶስ 10 (አዲሱ መ.ት)***

*¹ ወንድሞች ሆይ፤ አባቶቻችን ሁሉ ከደመናው በታች እንደ ነበሩና*

*በባሕሩ ውስጥ እንደ ተሻገሩ ታውቁ ዘንድ እፈልጋለሁ።*

*² እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ።*

ታዲያ ይህንን መነሻ ካደረግን አሁን ደግሞ *እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል-ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አማኞች የሚኖረው ጥቅም ምንድነው? ልንማር የሚገባንስ ነገር ምንድነው? ትርጓሜውስ ምንድነው?* እነዚህን ጥያቄዎች ይዘን እስቲ ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም ለሚኖሩ ክርስቲያኖች እና በገላቲያ ላሉ ክርስቲያኖች የጻፈውን መልዕክት እንመልከት፡-

***ሮሜ 4 (አዲሱ መ.ት)***

*¹ እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነ አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን?*

*² አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣ የሚመካበት ነበረው፤*

*ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት መመካት አይችልም።*

*³ መጽሐፍስ ምን ይላል? "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።"*

በሮም የምትገኘው ቤተ-ክርስቲያን መልዕክቱ መዝጊያ አከባቢ እንደምንመለከተው ከሆነ ከአይሁድ ወገን እና ከአህዛብ ወገን የሆኑ እንዳሉ ግልጽ ነው። የመልዕክቱ ዋና ነጥብ ደግሞ ኃጢአተኛው የሚጸድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ላይ ባለው እውነተኛ እምነት ሲሆን፤ ይህንንም በተለያየ መንገድ ይሞግታል፣ ያስተምራል። በመጀመሪያ ምንባብ እንደምንረዳው እግዚአብሔር ራሱን ያለምስክርነት ያልተወ ቢሆንም እንኳን፤ ሰዎች ግን ይህንን ምስክርነት ቸላ በማለት እውነትን በአመፃ አፍነው ያዙ። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ በእነዚህ ዓይነቶች ላይ ይገለጣል **(ሮሜ 1፥19-21)**። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል-ኪዳን በመግባት እስራኤልን ሕዝቤ ቢልም ለአህዛም ራሱን ያልገለጠ አምላክ አይደለም። ስለዚህ በአንድ ጎኑ እግዚአብሔር ጻድቅ በፍርዱም ትክክል ይሆናል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አሕዛብ ይህን ፍርድ ይቀበሉ ዘንድ የሚገባቸው፣ ማመካኛ የሌላቸው ሆነዋል**(ሮሜ 1፥20)**።

በሌላ መልኩ ደግሞ ይሁዲ ነኝ የሚሉትን በተመለከተ ጳውሎስ ፊቱን ዘወር ያደርግና ***"****አንተ ከአባቶች የተነሳ የተወደድክ ብትሆንም እንኳ አንተም እግዚአብሔር በሰጠው ሕግ እንደሚፈርድብህ አታውቅምን**?"*** በማለት ይጠይቃል። ምንም እንኳ ሕግ የእነርሱ ሆኖ በአህዛብ ላይ ቢሳለቁም ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው ያው በሕጉ ፊት ተላላፊ ናቸው **(ሮሜ 2፥17-24)** ።

*ታዲያ ዋናው ነገር ምንድነው**?*** ብለን ስንጠይቅ ዋናው ነገር የሕጉ ባለቤት መሆን አይደለም ***(****በእርግጥ እስራኤላዊ መሆን ጥቅም አለው**)**፤* እውነተኛ ይሁዲነት በሥጋ የአብርሃም ልጅ መሆን አይደለም፣ አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሲሆን ማለትም በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲሆን ነው።

ስለዚህ ማንኛውም የሮሜን መልዕክት የሚያነብ ሰው ወደ አንድ ድምዳሜ ይደርሳል ይህም ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ነው የእግዚአብሔርም ፍርድ ይገባዋል የሚል ድምዳሜ ነው። ሮሜ **3፥23** ***"****ሁሉም ኀጢአትን ሰርተዋል**"*** በማለት አይሁድም ሆነ አህዛብ በእግዚአብሔር ፊት ፍርድን የሚፈልግ እንደሆነ ይናገራል።

ይህ ለሰው ልጆች ሁሉ መጥፎው ዜና ነው። አንተ/ቺ፣ ሁላችንም ኀጢአተኞች ነን፤ ፍርድም ይገባናል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ መልካሙን ዜና ሲጀምር እንዲህ በማለት ነው፡-

<u>*ሮሜ **3** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*[21] አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል።*

*[22] ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም፤*

*[23] ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤*

*[24] በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤*

*[25] በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤*

*ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው፤*

ምንም እንኳን ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ቢሆኑም እንኳ፤ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን የማስተሰሪያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል፣ በዚህም መስዋዕት በማመን ብቻ ጽድቅ ይገኛል ማለት ነው።

አንባቢዬ ሆይ ረጅሙን ንባብ አብረኸኝ እንደመጣህ አያለሁ አሁን ወደ ሮሜ ምዕራፍ አራት ስንሄድ ጳውሎስ አንድ ሙግት ያቀርባል ይህ ሙግት አሁን ከዚህ በፊት ባልኩት ምንባብ ላይ ጳውሎስ ***"**አብርሃም ምን አገኘ**?"*** በማለት ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ አንባቢው ወዲያ በሥጋ አባታቸው የሆነውን አብርሃምን እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፤ ለዚህ ጥያቄ ደግሞ ዋቢ የብሉይ ምንባብ ደግሞ፡-

<u>ዘፍጥረት **15፥6** (አዲሱ መ.ት)</u>

***"**አብራም እግዚአብሔርን **(**ያህዌ**)** አመነ፤ እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት።**"***

የሚለው ነው፡፡

ስለዚህ በዚህ በሮሜ አግባብ ጳውሎስ የሮሜን መልዕክት ሲረዳ፣ አብርሃም እግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ አደርግሀለው ብሎ ሲናገርለት ይህ ሕዝብ በዘፍጥረት እየተወራለት ያለው በክርስቶስ በኩል ሊመጣ ሰላለው የአዲስ ኪዳን አማኞች ወይም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሲሆን፤ እርሱም በዚህ በእግዚአብሔር

የተስፋ ቃል ሲያምን ይህንን እምነት እግዚአብሔር ጽድቅ አድርጎ እንደቆጠረለት በመናገር ጽድቅ በእምነት ብቻ መሆኑን ያስገነዝበናል። ይህ ምንባብ በሌላኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አንድ አይነት ትርጓሜ ይዞ ቀርቧል፡-

*<u>ገላትያ **3** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*⁶ እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ **“**እርሱ እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።**”***

*⁷ እንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ አስተውሉ።*

*⁸ መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣*

*“አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ” በማለት ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው።*

*⁹ ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ሰው ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው።*

እኛ እንደ አብርሃም በእምነት የጸደቅን፤ አብርሃምም እንደ እኛ በእምነት የጸደቀ በመሆኑ እርሱ በዘፍጥረት የሁላችን ራስ ሆኖ ቃል-ኪዳንን ተቀብሏል። አብርሃም በእምነት ጽድቅን ተቀብሎ ደግሞም የዚህ ቃል-ኪዳን አካል የሆነም መንፈሳዊ በረከቶችን እኛን በመወከል ከእግዚአብሔር ተስፋን ተቀብሏል።

ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የአብርሃም የሥጋ ልጆች ስብስብ ሳትሆን በመንፈስ በሆነ መገረዝ የልብ ግርዘት የሆነላቸው የሕያዋን ቅዱሳን ሰዎች ስብስብ ናት። ታዲያ በሥጋ ስላለው በረከት በኢያሱ በኩል ምንም እንኳን ቢቀበሉም ይህ በረከት ለአዲስ ኪዳን አማኞች ሊወርሱ ሰላለው ሰማያዊ በረከት ማሳያ ነው።

የአብርሃም የሥጋ ልጆች የሆኑት ምንም እንኳን ወደ ከነዓን እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ ቢያስገባቸውም ያ ግን ሊመጣ ስላለው ዘላለማዊ እረፍት ጥላ እንጂ እውነተኛ ጥላ አይደለም። ይህ እረፍት ደግሞ በኢያሱ በኩል ሳይሆን፤ በክርስቶስ በኩል ሊሆን ያለ ዘላለማዊ እረፍት ነው።

*<u>ዕብራውያን **4** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*⁸ ኢያሱ ዕረፍትን ሰጥቶአቸው ቢሆን ኖሮ፣ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ሌላ ቀን ባል ተናገረ ነበር።*

*⁹ ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል፤*

*¹⁰ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚገባ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፣*

*እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል።*

ምንም እንኳን ይህ የበረከት ተስፋ ለአብርሃም ቢሰጠውም፤ እውነተኛ በረከት ግን ከላይ ሊሆን ያለ በሥጋ ለሆኑት ሳይሆን በመንፈስ ልጆቹ ለሆኑ ለእነርሱ እግዚአብሔር እየተናገረ እንደሆነ አብርሃም ተረድቷል። ስለዚህም አብርሃም ምድራዊዋን ከነዓንን፤ ማርን እና ወተትን የምታፈሰውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ከተማ እየናፈቀ ይኖር ነበር።

*ዕብራውያን **11** (አዲሱ መ.ት)*

*⁸ አብርሃም ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው ስፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ በእምነት ታዘዘ፤*

*ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም፣ እሺ ብሎ ሄደ።*

*⁹ በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ በተስፋዪቱ ምድር በእምነት ተቀመጠ፤*

*የተስፋውን ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ፤*

*¹⁰ ምክንያቱም መሠረት ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር።*

## ማጠቃለያ፡-

የአብርሃም በረከትን ስንመለከት በሁለት መንገድ መመልከት እንደሚገባን፣ በሁለትም መንገድ ልንማረው እንደሚገባን እያየን ነው። እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች በእምነት ከአብርሃም ጋር ወራሾች ነን ስንል መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እያልን ከሆነ፤ መጽሐፉ እያለ ያለው ምድራዊ እና ጠፊ ስለሆነው ነገር ሳይሆን ሰማያዊውን የማይጠፋውን ዘላለማዊ የሆነውን ነው። ይህም አሁናዊ በሆነው ምድር የተባረክንበት መንፈሳዊ በረከት ሲሆን፤ መፃውን ዓለም ደግሞ ሰማያዊዉን ልብሳችንን ልንወርስ ያለን

የእርሱ የአብርሃም ልጆች ከክርስቶስ ጋርም ወራሾች ነን። ስለዚህ የቃል እምነት መምህራን “ከአብርሃም ጋር ወራሾች ነን” ቢሉም እንኳ የአብርሃም በረከት፤ አብርሃም እንደተረዳው ይህንን ቁስ የሆነን ነገር ሳይሆን ሰማያዊ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር መንግስት እና የእርሱ መንፈሳዊ ልጆች ዘላለማዊ ወራሽነት ነው የሚያሳየው እንጂ ምድራዊ ስለሆነ በረከት አይደለም።

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ሦስት

### *"በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ተባርክናል"*

ያለፉት ክፍሎች (ክፍል **1** እና ክፍል **2)** ላይ በነበረን ዳሰሳ መልካም ጊዜን እንዳሳለፍን ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ደግሞ የቃል እምነት መምህራን ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በላይ በቃል እምነት መምህራን ተደጋግሞ/ተዘውትሮ ሲጠቀስ የምንሰማውን ክፍለ ምንባብ የምንቃኝ ይሆናል።

የቃል እምነት ትምህርትን መሠረታቸው ያደርጉ ቡድኖች (ቤተ-ክርስቲያን የሚለውን ቃል ያልተጠቀምኩት በምክንያት ነው) በየመርሃ ግብራቸው መጀመሪያ ላይ የቃል ማውጣት **(Confession)** ጊዜ ሲኖራቸው፤ ***"እኔ እንዲህ ነኝ፣ እኔ እንዲያ ነኝ"*** ሲሉ ከእነዚህ ንግግሮች ውስጥ ***"እኔ የተባረኩ ነኝ" (I am blessed)*** ብለው ቃል ያወጣሉ። ይህንንም የሚሉበት መሠረት ልክ እንደ ሁል ጊዜው ከአውዱም ሆነ ከሌሎች የቅዱሳት አስተምህሮ በተፋቱ ምንባባት ላይ በተመሰረተ የተሳሳተ *ሥነ-* ትርጓሜ ነው።

በቃል እምነት መምህራን ዕሳቤ እግዚአብሔር ፈውስና እና ብልጽግናን ለክርስቲያኖች ቃል ገብቷል ታዲያ ከአማኞች የሚጠበቀው በእምነት ይህንን አምኖ መቀበል ነው። አምኖ መቀበል ምን እንደሆነ የዚህ ኑፋቄ መምህር ብስራት ብዙአየሁ(ጃፒ) ***"እምነት"*** በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ትምህርት ***"እምነት በሕይወታችን የሚሰራው በመናገር ነው፣ የምንናገረው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ነው"*** በማለት አስተምሯል። ስለዚህ እነዚህ እነርሱ **"**እግዚአብሔር አደረገልን**"** የሚሏቸው ፈውስ ሆነ **"**ብልጽግና**"** የራሳቸው ለማድረግ ***"ቃል ማውጣት"*** ብለው በሚጠሩት መሳሪያ ነው።

ብስራት ብዙአየሁ (ጃፒ) በድፍረት ይህንን ሲናገር፦ ***"ይህ አይነት እምነት እና አሰራር የእግዚአብሔርም ነው"*** በማለት ነው የሚያስተምረው። ማለትም እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ካለመኖር ወደመኖር ሲያመጣ አምኖ በመናገር ነው፤ ስለዚህ እኛም ልክ እንደሱ እምነታችንን ታምነን የሌለን ነገር

እንጠራለን፤ ይህንንም እምነት በማለት ይጠራሉ ብስራት ብዙአየሁ እና ሓራጥቋ መናፍቃን፣ ወገኖቻቸው።

ይህንን ዓይነት ሐሳብ በሁለት መንገድ እንሞግት ዘንድ ይገባል። የመጀምሪያው የሚጠቅሷቸውን ጥቅሶችም የሥነ-ትርጓሜ መርሆችን ተከትለን የምንባቦቹን ትርጓሜ በፍታቴ በማመልከት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎችን እንደነሱ ደግሞ ደጋግሞ ማወጅን ከቅዱሳት ሐዋርያት እና ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ልምምድ ጋር በማስተያየት፣ በእውነት ይህ ልምምድ ለቤተ-ክርስቲያን መጤ ነው ወይስ የነበረ**?** ሚለውን በማየት ቀጥተኛ **(Orthodoxy)** ወይም ወልጋዳ ብለን እንፈርጃለን።

አሁን እስቲ የኤፌሶንን ምንባብ በመመልከት፤ ትርጓሜውን ይዘን የመልዕክቱ ጸሐፊዎች ለመጀመሪያው ተደራሲያን ከመልዕክታቸው ይለማመዱ ዘንድ የሚያዟቸውን ነገር እንቃኝ።

<u>*ኤፌሶን **1፥3** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን*

*የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤"*

ይህንን ምንባብ በመጥቀስ የመጀመሪያ የሚያደርጉት ነገር የዓረፍተ ነገር አወቃቀሩ በመመልከት ነው ወደ ስሁት ድምዳሜያቸው የሚሄዱት። *"የባረከን"* የሚለው ቃል ጳውሎስ በዚህ ቦታ ሲጠቀም በአላፊ ጊዜ **(Past tense)** ነው። በዚህ ቦታ መባረካችን የተረጋገጠ ሲሆን፤ ይህንን በእምነት በመቀበል በማወጅ **(Confess)** በማድረግ በበረከት መመላለስ ነው።

በእርግጥ ይህ ምንባብ የሚገኘው ከላይም ከታችም ሌላ ነገር ሳይባል ቢሆን ብለን ብናስብ እንኳን ይህንን ዓይነት ትርጓሜ እና ወደ ደምዳሜ ለማስኬድ የሚያስደፍር ምን ነገር ይኖራል**?** ከንቱ የልብን ሐሳብ ወደ ቅዱሱ መጽሐፍት ለማስረግ ካልሆነ በስተቀር**?** ፤ እስቲ እንደሁል ጊዜያችን ቁጥሮችን ከፍ እና ዝቅ ብለን በአውዱ ፍታቴ ሰርተን ምልልስ ጋር አቆራኝተን የዛሬውን እንጨርስ።

*<u>ኤፌሶን **1** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*³ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን*

*የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤*

*⁴ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣*

*⁵ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን፤*

*⁶ ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው።*

*⁷ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት፣ የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን፤*

*⁸ ጸጋውንም በጥበብና በማስተዋል ሁሉ አበዛልን።*

*⁹ በክርስቶስ ያቀደውንም የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሐሳቡ እንድናውቅ አደረገ።*

*¹⁰ በዘመን ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ*

*ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።*

ይህ የኤፌሶን መልዕክት ተብሎ በአማርኛ የተጠቀሰልን መልዕክት ዟሪ ደብዳቤ እንደሆነ ሊቃውንት ይስማማሉ። ማለትም ልክ የሰርግ መጥሪያ ወረቀት ላይ ለ___________ ተብሎ በባዶ ቦታው የተደራሲው ስም እንደሚገባ ሁሉ፤ ይህ መልዕክትም ለአንድ ቦታ የተጻፈ ሳይሆን የሚዞር መልዕክት ነው። ይህ ደብዳቤ በመግቢያ ቁጥሮች ላይ (ከቁጥር **1-2**) ላይ ስለ ጸሓፊው ማንነት እና ሐዋርያዊ ስልጣን እና የተደራሲዎች ማንነት የያዘ ነው (በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉ፣ ለታመኑ እና ቅዱሳን) በማለት ሰላምታ አቅርበላቸው ይጀምራል፤ በዚህም አጻጻፉን ይጀምራል።

ቀጥሎ ደግሞ *"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እና አባት የሆነ አብ በመንፈሳዊ በረከት ደግሞ ባርኮናል"* በማለት ለዚህም መንፈሳዊ በረከት ባራኪ እግዚአብሔር አብ ምስጋና ያቀርባል (ቁጥር **3**)

ሶስት ነገሮችን እንረዳለን፡-

i) የባረከን አብ

ii) የተባረክነው በክርስቶስ በኩል

iii) የበረከቱ አይነት መንፈሳዊ በረከት

እነዚህ በረከቶች ምን ምን ናቸው? ስንል ቀጥሎ ጳውሎስ በመገረም እና በመደነቅ የሚዘረዝራቸው ነገሮች አሉ። እነዚህም በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ የመዳናችን በረከቶች ተብለው የሚታወቁ ናቸው። እስቲ በረከቶቹን እንመልከት፡-

***i) መርጦናልና (ቁጥር 4)***

አማኞች ልክ እንደሌሎች በበደላቸው በኀጢአታቸው ምክንያት ሙታን፣ የዓለምንም ክፉ መንገድ የተከተሉ፣ ለክፉ መንፈሳዊያን አለቆች የሚገዙ፣ የሥጋቸውን ምኞት ሲፈጽሙ በምድር ሲኖሩ የነበሩ ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳን እና አለነውር(ነውር አልባ) ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸው ናቸው። መመረጣችንን መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምር እግዚአብሔር አብ እንደመረጠን እና ወልድ ቤዛ ይሆነን ዘንድ እንደመጣ ያስተምራል

*<u>ዮሐንስ **17** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*² ከአንተ ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጥ*

*በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥተኸዋልና።*

*³ እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም*

*ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።*

**…**

*⁶ "ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገልጬላቸዋለሁ።*

*የአንተ ነበሩ ለእኔ ሰጠኸኝ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል።*

*⁷ የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ አሁን ዐውቀዋል፤*

*⁸ ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸው ተቀብለዋል፤ እኔም ከአንተ እንደ ወጣሁ*

*በርግጥ ዐውቀዋል፤ አንተ እንደላክኸኝም አምነዋል፤*

*⁹ እነርሱ የአንተ ስለሆኑ እጸልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም።*

ተጨማሪ ምንባባት **(**ማቴ **11፥25** ዮሐ **6፥44 6፥65** ዮሐ **10 ፥11** ሐዋ **20፥28-29** ኤፌ **5፥25)**

ስለዚህ የመዳናችን ነገር እንደው ያልታቀደ ድንገተኛ ሳይሆን፤ ዓለም ሳይፈጠር በሥላሴ ሕብረት የታቀደ፣ የአሃዱ ሥሉስ አምላክ ንድፍ **(Plan)** ነው። በዚህም የዚህ ዕቅድ ንድፍ አውጪ የሆነው እግዚአብሔር አብ ይባረክ ይለናል ሐዋርያው ጳውሎስ።

***ii)*** *ልጆቹ እንሆን ዘንድ ወሰነን* ***(****ቁጥር* ***5)***

በዚህ ስፍራ ከላይ ካቀረብኩት ማብራሪያ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር በክርስቶስ የመስቀል ሞት ቅዱሳን እና ነውር አልባ ካደረገን በኋላ፤ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን መወሰኑን፣ ይህ ሌላኛው የእግዚአብሔር አብ ዕቅድ ነው። ጊዜውም ሲደርስ በወንጌል አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ዳግም ልደትን ተቀብለን በእምነት አማካይነት ለእርሱ ልጆች ሆነናል። ይሁን እንጂ ይህ ግን የአሃዱ ሥሉስ አምላክ ዘላለማቂ ዕቅድ ነው፤ ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር አብን ይባርካል።

***iii)*** *እንዲያው በነጻ ተወደናል* ***(****ቁጥር* ***6)***

ከላይ ያነሳቸውን ሁለት ነገሮች ለምን አደረገ**?** በምድር ላይ እንደኔ ያሉ ኀጢአተኞች ብዙ ናቸው፣ በየሰከንዱ እና በየደቂቃው በሚሊዮን የሚቆጠሩ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች ወደ ሲዖል ይሄዳሉ፤ ታዲያ እኔ የዳንኩት ለምንድነው**?** በእኔ ዘንድ ምን ለመዳን ምክንያት አለ**?** ብለን ይህንን ጥያቄ ስንጠይቅ ያኔ ሐዋርያው ጳውሎስ ለምን እንደሚያመሰግን ይገባናል፤ ክቡር የሆነው ጸጋው ይመሰገን ዘንድ**!**

***iv) ቤዛነትን አገኘን (ቁጥር 7)***

ቤዛ ማለት የተያዘን ወይም የተወሰደን ነገር/ንብረት ለማስመለስ የሚከፈል ዋጋ፣ ካሣ፣ ለውጥ ነው። ለምሳሌ፡- ገንዘብ የሕይወት ቤዛ ነው **(ምሳሌ 13፥8)** የእስራኤል ሕዝብ ቤታቸውን ወይም መሬታቸውን ከሸጡ በኋላ ለመቤዠት ይችሉ ነበር።

ቤዛ የሚለው ቃል ከነጻነት ጋር የተያያዘ ነው። ሁላችንም የኃጢአት ዕዳ አለብን፤ የኀጢአት ደሞዝ ደግሞ ሞት ነው። ሁላችምም ይህንን ሞት የሚገባን ብንሆንም ነገር ግን በእኛ ምትክ ሞታችንን በሞተልን ከዕዳችን ነጻ ባወጣን በእርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ በኩል ቤዛነታችንን አገኘን። ይህም የአሃዱ ሥሉስ አምላክ ዘላለማዊ ዕቅዱ ነውና ***"ለእርሱ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሁን"*** ይለናል ሐዋርያው ጳውሎስ።

***v) የኃጢአትን ይቅርታ አገኘን (ቁጥር 7)***

ምንም እንኳ ኃጢአታችን እጅግ የላቀ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን አንዲያ ልጁን ልኮልን የኀጢአትን ይቅርታ አድርጎልናል። በዚህም ምክንያት እኛ አማኞች አሁን ከእግዚአብሔር አብ ጋር ሰላም ነን **(ሮሜ 5፥1)** ፣ አባ አባ ብለንም የምንጮህበትን ድፍረት ተቀብለናል **(ሮሜ 8፥15)** ፣ አሁን የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነን **(ኤፌ 2፥20)** እንጂ እንግዶች እና መጻተኞች አይደለንም።

ታዲያ ይህ ሁሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በሠማያዊው ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት እንዴት እንደተባረክን እያወራ አይደለም ወይ**?** እንቀጥል

***vi) ጸጋውንም በጥበብ እና በማስተዋል አበዛልን (ቁጥር 8)***

ይህ የአምላካችን ጸጋ በሕይወታችን ጥበብ እና ማስተዋልን የሚያበዛልን ነው።

***1ኛ ቆሮንቶስ 2 (አዲሱ መ.ት)***

*[12] ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤*

*ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው።*

...

*¹⁴ መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤*

*ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤*

*በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ፣ ሊረዳው አይችልም።*

የእግዚአብሔርን ነጻ፣ ስጦታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያወቅነው ከሌሎች ሁሉ የተሻልን ጠቢባን ስለሆንን ነው**?** አይደለም። ሌሎችስ ይህንን የእግዚአብሔርን ስጦታ የማይቀበሉት ከእኛ ይልቅ ያልተማሩ በመሆናቸው ነው**?** በፍጹም አይደለም**!** የእግዚአብሔርን ነጻ ስጦታ እናውቅ ዘንድ መንፈሱን በልባችን ያኖረ እግዚአብሔር አብ ራሱ ስለሆነ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሥራ ምስጋናን የሚያቀርበው።

***<u>1ኛ ዮሐንስ 5፡20 (አዲሱ መ.ት)</u>***

*“የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛ የሆነውን*

*እርሱን እንድናውቅ ማስተዋልን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤*

*እኛም እውነተኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አለን።*

*እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።*

***vii) የፈቃዱን ምስጢር እንድናውቅ አደረገ (ቁጥር 9)***

እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ በኩል ብዙ ነገር አድርጎልናል። እዚህ ቦታ ላይ ከላይ ካልነው በተለየ መንገድ *የፈቃዱን ሚስጢር* እናውቅ ዘንድ አድርጎናል። ይህ ምን ዓይነት መታደል ነው**?** እግዚአብሔር ለቤተ**-**ክርስቲያን ሊያያደርግ ያለውን ዕቅዱን ምን እንደሆነ ለሕዝቡ አሳውቋል። ይህም ሐሳቡ *“በዘመን ፍጻሜ*

*ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው"* ይለናል ሐዋሪያው ጳውሎስ። **(**ቁጥር **10)**

ታዲያ የዚህ ምንባብ ትርጉም በምንም መልኩ/ሒሳብ ሰማያዊውን ስጦታ ከምድሩ ጋር እናያይዝ**?** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍለ**-**ምንባብ ስለ ቤት፣ መኪና ወይም ስለ ብልጽግና የሚያስተምረው ነገር አለ**?** ይህን ዓይን ያለው **(**ክርስቲያን ያልሆነ ሁሉ**)** ሊያይ ቢችልም እኛ ዳግም የተወለድን አማኞች ግን እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ በኩል እንዴት እንደ ባረክን እናያለን እንጂ እንደነዛ መናፍቆች *"በረከት"* የሚል ቃል እያሳደድን ከንቱ እና ጠፊ የሆነውን ከዘላለማዊው ጋር በንፅፅር ማቅረብ የምድሩን ማክበር ሳይሆን፤ የሰማዩን ጎትቶ ከንቱ እና ውዳቂ ማድረግ ነው።

ወደ ሁለተኛው ደግሞ ስንሄድ፡**-** እነዚህን ምንባባት ትክክለኛ ትርጓሜ ይዘናል፤ ታዲያ እነዚህን ምንባባት በማወጅ **(Confess** በማድረግ**)** አንዳች መንፈሳዊ ዕድገት ይመጣብን ይሆን**?** ይህንን ልምምድ ጳውሎስ ያዘናል ወይ**?** በፍጹም**!** በፍጹም አያዝም**!**፤ ይልቅ እንዲህ ይላል፡**-**

<u>*ኤፌሶን **4፥1** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"እንግዲህ በጌታ እስረኛ የሆንሁ እኔ፣*

*ለተቀበላችሁት ጥሪ የሚገባ **ኑሮ ትኖሩ** ዘንድ እለምናችኋለሁ።"*

<u>*ኤፌሶን **4፥17** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"ስለዚህ ይህን እነግራችኋለሁ፤ በጌታም ዐደራ እላለሁ፤*

*በአስተሳሰባቸው ከንቱነት እንደሚኖሩት እንደ አሕዛብ ልትመላለሱ አይገባም።"*

<u>*ኤፌሶን **5** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*[1] እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤*

*[2] ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት*

*አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።*

**...**

*[15] እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ።*

**...**

*[17] ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ።*

*[18] በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና።*

**...**

*[22] ሚስቶች ሆይ፤ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁም ተገዙ*

**...**

*[25] ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም*

*ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤*

*ኤፌሶን **6** (አዲሱ መ.ት)*

*[1] ልጆች ሆይ፤ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤ ይህ ተገቢ ነውና።*

**...**

*[5] ባሪያዎች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምት ታዘዙ፣ በምድር ጌቶቻችሁ*

*ለሆኑት በአክብሮትና በፍርሀት፣ በልብ ቅንነትም ታዘዙ፤*

**...**

*⁹ እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ የእነርሱም፣*

*የእናንተም ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ፣ የሰውንም ፊት አይቶ እንደማያደላ*

*ታውቃላችሁና አታስፈራሯቸው።*

ስለዚህ አንባቢዬ ሆይ እነዚህ ሓራጥቋ መናፍቃን ትርጉም ሆነ ልምምዳቸው ከቃሉ የተፋታ፣ ይልቅ ስሜት ላይ እና ስነ ልቦናን ማነቃቃት ላይ የተመሠረተ አይደለምን**?**

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል አራት

### *"በመገረፉ ቁስል ተፈውሰናችኋል"*

ይህንን ምንባብ/ጥቅስ ስታነቡ አስቀድሞ ወደ ልባችሁ የሚመጣው ምንድነው? እኔ ድሮ ድሮ ይህንን ምንባብ በሕሊናዬ የማስበው ታምሜ፣ አሊያም ደግሞ ሰዎች ታመው ላጽናና ስሄድ ይህንን ምንባብ አስባለሁ። ይህንን ምንባብ እንዴት እንደዚህ ልረዳው እንደቻልኩ ባላስታውስም፤ ምናልባት በየምታተ መስኮቱ (ቴሌቪዢን) ያሉ *"ሰባኪዎች"* እና እንዲሁም ደግሞ ከየአውደ-ምህረቱ/ከየመድረኩ ምንባቡ ሲብራራ፤ ይህንን ምንባብ አካላዊ በሽታን ኢየሱስ ተሸክሞልን እንደሞተ፣ እኛም ከዚህም ስጋዊ በሽታ እንደተፈወስን በተደጋጋሚ ስለተነገረኝ ይመስለኛል። ነገር ግን የቃሉ ፍቺ የእውነት እንደዚያ ነው? ይህንን ጥያቄ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ጠልቄ ሳጠና ልክ እንዳልነበርኩ አሰተውያለሁ።

እንደ አጋጣሚ የእኛ መሳሳት ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እንደ እንጉዳይ የሚፈሉ ሓራጥቋ መናፍቃን በየ ጊዜው እየቀረቡ ሲለፍፉም፤ የዚህ ክፉ ትርጓሜ እና ስሁት ድምዳሜ ሰለባ የሆኑ ሰዎችን በዛት ቤቱ ይቁጠረው። በአንድ አጋጣሚ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ከአንዲት እህቴ ጋር ስናወራ አባቷ የዚህ ክፉ ምንፍቅና ሰለባ ከመሆኑ የተነሳ ቤት ውስጥ ሰው ታሞ እንኳ *"በመገረፉ ቁስል ተፈውሰናችኋል"* በማለት ወደ ሕክምና ተቋም አይወስዷቸውም ነበር። እንደምንም ብለው ዘመድ ከወሰዷቸው ደግሞ ልክ እንደ ኢ-አማኒ ይመለከቱም ነበር። እግዚኦ!

እስቲ ክፍለ ምንባቡን እንመልከትና ወደ ትንታኔው እንግባ፤ መልካም ንባብ።

<u>*ኢሳይያስ **53** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*4 በርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤*

*እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው።*

*[5] ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤*

*በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።*

እስቲ እንደ ሁል ጊዜው አስቀድመን የዚህ መልዕክት ቀዳማይ ተደራሲያን፣ የመጽሐፉ ሰዎች አይሁዳዊያን መልዕክቱን እንዴት እንደ ሚተረጉሙት እንመልከት፡-

ይህንን ምንባብ አይሁድ እንዴት ሊረዱ እንደሚችሉ መንደርደሪያ አድርጌ ልነሳ የፈለኩት የጌታችንን ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ የጻፈውን በመመልከት ሲሆን፤ ቀጥሎ ደግሞ በመልዕክታት ውስጥ የዚህ ክፍል ትርጓሜ በሐዋርያው ጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ የተሸከመው ትርጉምን በመጠቆም ወደ ድምዳሜ መሄድ ነው።

ማቴዎስ በወንጌሉ ውስጥ *"ይፈጸም ዘንድ"* እና *"ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ"* የሚሉ ንግግሮች ወደ **17** ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር፣ ማቴዎስ ለተደራሲያኑ ኢየሱስ እርሱ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመሰከሩለት መሲሑ መሆኑን ያውጃል፡፡

*<u>ማቴዎስ **8** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*[14] ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት ጎራ ሲል*

*የጴጥሮስ ዐማት በትኵሳት ታማ ተኝታ አገኛት።*

*[15] እጇን ዳሰሳት፤ ትኵሳቱም ለቀቃት፤ ተነሥታም አገለገለችው።*

*[16] በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤*

*እርሱም መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ።*

*[17] በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤*

*"እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ።"*

እነዚህ ከብሉይ ኪዳን የሚጠቅሳቸው ምንባባት በሙሉ የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር እርሱ በቅዱሳት መጽሐፍ የተመሠከረለት መሲሑ ነው የሚል ሙግት ማቅረቡ ነው። ማቴዎስ *“ጌታ ኢየሱስ የጴጥሮስን ዐማት ፈወሰ፤ በዚያው ምሽት ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው እነዚህን ሁሉ ኢየሱስ ፈወሰ፤ በዚህም ነቢዩ ኢሳያስ ስለ ጌታ መሲሑ ኢየሱስ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ”* ይለናል።

ልብ ማለት ያለብን በዚህ ቦታ ማቴዎስ ይህንን ሲናገር ገና የመስቀል ሞትን ያልሞተው፤ ይልቅ በሕይወቱ እያለ ይህንን ትንቢት በዚህ ፈውስ መፈጸሙን እያሳየን ነው። ስለዚህ በዚህ በማቴዎስ ምንባብ ውስጥ ማንም ሰው የክርስቶስን መስቀል በማመልከት የኢሳያስን ትንቢት ለማመሳከር ቢሞክር ይህ ከማቴዎስ ምንባብ ጋር ትክክል አይሆንም ማለት ነው። ይልቅ ትንቢቱ የተፈጸመው የጴጥሮስን ዐማት በፈወሰበት ዕለት ሲሆን፣ በአይሁዳዊያን ዘንድ በተገለሉ ማሕበረሰብ ማንም ሊነካቸው የማይፈልጋቸውን የአይሁድ ሰዎችን በእጁ በመዳሰስ፤ ይህ መሲሕ በኢሳያስት የተነገረለት እርሱ ለሕዝቡ የሚያዝን፣ ሕዝቡን የሚወድ መሆኑን በማሳየቱ፤ ማቴዎስ *“እርሱ መሲሑ ነው”* እያለን ነው። ስለዚህ ቀዳማይ ተደራሲያን ሊረዱ በሚችሉበት አግባብ ወንጌላዊው ማቴዎስ *“ይህ ይመጣል የተባለው ነቢዩ ኢሳያስ የተነበየለት እርሱ ደዌያቸውን እና ሕመማቸውን ይቀበላል የተባለለት መሲሕ ኢየሱስ ነው”* እያለ ነው።

ይህ ክፍለ-ምንባብ (ምዕራፍ **8)** ጌታ ኢየሱስ ብዙ አይነት ሰዎችን የፈወሰበት እና ተዐምራትን ያደረገበት ነው።

- ለምጻሙን ሰው ፈወሰ **(8፥1)**
- የመቶ አለቃው አገልጋይ ሽባውን ሰው ፈወሰ **(8፥5-13)**
- ኢየሱስ የጴጥሮስን አማት ፈወሰ **(8፥14)**
- በአጋንንት የተያዙ ሰዎችን ፈወሰ **(8፥16)**
- በሽተኞችን ሁሉ ፈወሰ **(8፥16)**

ማቴዎስ ይህንን ሁሉ ሲመለከት፤ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን በግልጽ በእጁ ዳስሶ ሲፈውስ፣ ሁለቱን ደግሞ ቃል በማውጣት ፈውሷል፤ ምናልባት ደግሞ በሽተኞች የተባሉትን በምን መልኩ እንደፈወሰ ሳይናገር ግን እንደፈወሳቸው ብቻ ይናገራል። በመጀመሪያ የተፈወሰውን ሰው የተመለከትን እንደሆነ በለምጽ የታመመ ነው። ስለ ለምጽ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

*__ዘሌዋውያን **13** (አዲሱ መ.ት)__*

*[1] እግዚአብሔር **(ያህዌ)** ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፤*

*[2] "ማንኛውም ሰው በሰውነቱ ቈዳ ላይ ዕብጠት ወይም ቾፍታ ቋቍቻ*

*ቢወጣበትና ይህም ወደ ተላላፊ የቈዳ በሽታ የሚለወጥበት ከሆነ፣*

*ወደ ካህኑ አሮን ወይም ካህናት ከሆኑት ልጆቹ ወደ አንዱ ያምጡት።*

*[3] ካህኑም በሰውየው ቈዳ ላይ ያለውን ቍስል ይመርምር፤ በቍስሉ በተበከለው አካባቢ*

*ያለው ጠጕር ወደ ነጭነት ተለውጦ ቢያገኘውና በታው ጐድጐዶ ወደ ውስጥ ቢገባ፣*

*ይህ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው። ካህኑም መርምሮ ይህን ባወቀ ጊዜ፣*

*ሰውየው በአምልኮው ሥርዐት መሠረት ርኩስ መሆኑ ይገለጽ።*

**(በተጨማሪ ዘሌ 13፥45-46፣ 52+57)**

ለምጽ ተላላፊ የቆዳ በሽታ ነው፤ የሚተላለፈው ደግሞ በንኪኪ ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ግን ይህንን በሽታ የታመመውን ሰው ዳስሶ ፈውሷል። ማቴዎስ በወንጌሉ የነቢዩን ኢሳያስ ትንቢት በማምጣት "እርሱ ኢየሱስ የዚህ ትንቢት ፈጻሚ ነው" ብሎ ይመሰክራል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን ትንቢት በተመለከተ ሲናገር፡-

*__**1**ኛ ጴጥሮስ **2** (አዲሱ መ.ት)__*

*[24] ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን*

*በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል እናንተ ተፈውሳችኋል።*

*[25] ቀድሞ እንደ ጠፉ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።*

ጴጥሮስ የዚህን ትንቢት ፍጻሜ ከአማኞች ደህነት ጋር የተያያዘ እንጂ ከምድራዊ ጤንነት ሆነ የብልጽግና ተስፋ ጋር አልተቆራኘም። ለምግባረ ብልሹነት ግብዣ እየቀረበላቸው ላሉ አማኞች ጴጥሮስ በምትካዊ ሞት ትምህርት አማካይነት **"**እኛ በበደላችን እና በኃጢአታችን ሙታን ነበርን በማለት እርሱ የእኛን ሞት በመተካት በመሞቱ፤ የእርሱ ሞት የእኛ ሞት አድርጎ በመቁጥር፤ ትንሳዔው ደግሞ የእነርሱ እንደሆነ በመቁጠር እርሱ **[**ኢየሱስ ክርስቶስ**]** በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከሞ የኀጢአትን ይቅርታን ለእኛ በማስረገጥ ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቃችንን እውነት ደግሞ በትንሳዔው አወጀ። ይህ ደግሞ ለአማኞች የሚኖረው እንድምታ **(Implication)** የኃጢአትን ግብዣ እምቢ ብለን በቅድስና እንኖር ዘንድ ነው።

ኢሳያስ የመሲሑን ሕዝቦች እንደ በግ፤ መሲሑን ደግሞ እንደ እረኛ ምሳሌ አድርጎ ሲናገር፤ ጴጥሮስም ተመሳሳይ አገላለጽ በመጠቀም፣ አስቀድመን እንዴት ባለ ሁኔታ የጠፋን እንደነበርን፤ ነገር ግን የነፍሳችን እረኛ **(**ምትካዊ ሞታችንን የሞተልን**)** እርሱ እንዳገኘን ይመሰክራል። **(1**ጴጥ **2፥25)**

ታዲያ እነዚህን ምንባባት እንዴት ባለ ትርጓሜ ብንረዳ ይሁን፤ ከስጋ ፈውስ ጋር አቆራኝተን ስንታመም ይህንን ጥቅስ የምንጠቅሰው**?** የቃል እምነት መምህራንስ ይህንን ምንባብ በምን ዓይነት መንገድ ቢተረጎሙት ነው፤ አንታመም በማለት ከንቱ ቅዠታቸውን የሚነዙት**?**

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል አምስት

### *"በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ" 2ቆሮ 8፥9*

በዚህ ክፍል ደግሞ በ**2**ኛ ቆሮንቶስ ላይ የሚገኘውን ምንባብ የምንቃኝ ሲሆን፤ አስቀድመን የቃል እምነት መናፍቃን በዚህ ምንባብ ላይ ያላቸውን የተጣመመ ትርጓሜ ካየን በኋላ፤ ቀጥለን ደግሞ አውዱን የጠበቀ እና የሥነ-ትርጓሜ መርሆችን በተከተለ አግባብ ፍታቴ በመሥራት የዚህን ምንባብ ትርጉም እናያልን፤ በስተመጨረሻ ለቃል እምነት መምህራን ጥያቄ በማቅረብ ይህንን ክፍል እንጨርሳለን። መልካም ንባብ**!**

ባለፈው ባየናቸው ምንባባት **(**ክፍሎች**)** የቃል እምነት መምህራን *"ክርስቲያን አይታመም፣ ክርስቲያን በገንዘብ ሊደኽይ አይችልም"* ለማለት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ አይተን ነበር። ከእነዚህም በክፍል ሦስት ላይ ኤፌ **1**፥**3** ላይ ያለውን መንፈሳዊ በረከት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ጽፌ ነበር።

የቃል እምነት መምህራን እነዚህን በረከት የሚሉ ቃላቶችን ሲያገኙ ሁልጊዜ የሚሰጡት ትርጉም ምድራዊ በረከት ጋር ሲያቆራኙ፣ የመጽሐፉን ትርጓሜ ሲያንጋድዱ እና ከእውነቱ ሲስቱ ነው የምናየው።

ብስራት ብዙአየሁ በ**"New Creation International 'Church'** *<u>የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኛ መለኮታዊ ፈውስ እና መለኮታዊ ጤንነት</u>"* በሚለው ርዕስ ሲያስተምር በአንድ አጋጣሚ ከበድ ያለ የጤና መታወክ አጋጥሞት እንደነበር ይመሰክራል፤ በዚህም ብቻ አልቆመም። በሽታውም ጸንቶበት የሞት ድምጽ መስማት ጀምሮ እንደነበር እያስታወሰ ለሕዝቡ ይህንን ሁኔታ ስለቀየረበት ሁኔታ ይናገራል፤ በመጀመሪያ *"በኢየሱስ ስም"* እያለ በሽታውን ሲያስታገስ ከርሞ የነበረ ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ በሽታው

እየመጣበት እንደሚያስቸግረው ተናግሮ፤ በመጨረሻው ግን በሽታው ላይ በኃይል እንደተገለጠበት በመናገር ተፈውሻለሁ ይለናል።

እንዲህ ያለ ምስክርነት ከአስተምህሯቸው ጋር የሚጣረስ መሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም እነርሱ በዋናነት ***"እግዚአብሔር በክርስቶስ ላት የገባው ቃል-ኪዳን ነው"*** ከማለታቸው፤ እንዲሁም ደግሞ ለዚህ ቃል-ኪዳን መፈጸም በክርስቶስ መሆን ዋነኛው ቁልፉ ነገር ከመሆኑ አንጻር ጃፒ በእነዚህ አይነት ችግሮች ማለፉ ክርስቲያን ላለመሆኑ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ አይችልምን**?** ነው ወይስ ክርስቲያን ያውም መምህሩ ራሱ ይታመማል**?**

የዚህ ትምህርት ሌላኛው መገለጫ ደግሞ ***"Devine prosperity"*** ነው፤ መለኮታዊ ብልጽግና የሚሉት ማለት ነው።

በአንድ አጋጣሚ አንድ የቃል እምነት ሰባኪ ሲናገር ***"ኢየሱስ ስለ እኛ ብሎ ደሃ ሆኖ ነበር፣ እኛ ደግሞ ባለጠጎች እንሆን ዘንድ"*** በማለት ይህንን ምንባብ እያነሳ ያስተምር ነበር፤ ለመሆኑ የዚህ ምንባብ ኃሳብ ይህ ነው**?** ቀጥሎ እንመልከት፡-

<u>***2ኛ ቆሮንቶስ 8፥9 (አዲሱ መ.ት)***</u>

*"የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤*

*በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ*

*እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድኻ ሆነ።"*

የጳውሎስ ሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ በይሁዳ ለሚኖሩ ቅዱሳን እርዳታን ይዞ የመሄድ ዓላማን ያነገበ ነበር። ይህም እርዳታ ነቢዩ አጋቦስ በይሁዳ ሊነሳ ስለነበረው ድርቅ በመናገሩ ምክንያት ያ ድርቅ በይሁዳ መከሰቱ ነበር። **(ሐዋ 11፥27-30)** እንዲሁም ጳውሎስ በሮሜ **15፥25-28** ላይ ይህንን አገልግሎት

ለወንድሞች ይደረግ ዘንድ ያሳስባል። በገላቲያ **2፥10** ላይ በኢየሩሳሌም ያሉ እንደ አዕማድ የሚታዩት ኬፋ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ እና ጳውሎስን አደራ ያሉት ነገር ቢኖር ድኾችን ማሰባቸውን እንዳይተዉ ነው።

ስለዚህ እነዚህ በቆሮንቶስ ያሉ አማኞች፣ በይሁዳ ያሉ ሌሎች አማኞች ላይ ድርቅ ከመነሳቱ የተነሳ በመቸገራቸው ምክንያት አንደኛ ራሳቸው ደቀ መዛሙርቱ በማዋጣት ቀጥሎ ደግሞ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ያዋጡ ዘንድ ማሳሰቡ ነው። የ**2**ኛ ቆሮ ምዕራፍ **8** ታሪካዊ ዳራ ይህ ነው።

የቆሮንቶስ ሰዎች ግን ለዚህች ቤተ-ክርስቲያን በራስ-ተነሳሽነት ለማድረግ ግን ሰነፎች ነበሩ፤ ስለዚህ ይህ ደብዳቤ በይሁዳ ለሚገኙ ደኻዎች ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር እያስተማረ ነው። መስጠት እንደሚገባቸው ለቆሮንቶስ ሰዎች ለማስተማር የተጠቀመበት መንገድ ሌሎች የሰጡትን የመቄዶንያ ሰዎች ምሳሌ አድርጎ በማቅረብ ነው።

በዚህ ምንባብ ምሳሌ ሆነው የቀረቡትን የልግስና ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

***i)*** *የመቄዶንያ ሰዎች*

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መቄዶንያ ቤተ-ሰዎች የሚሰጠው ምስክርነት አስገራሚ ነው። ***“. . .*** *በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለ ጠግነት አብዝቶአል፤* ***. . .”*** **(2** ቆሮ **8፡2)** ይላል። የመቄዶንያ ሰዎች ምንም እንኳ ለራሳቸው ድሃዎች ቢሆኑም ነገር ግን ለወንድሞች ያላቸው ፍቅር የሚገርም ነው። አሁን እንኳ ያደረጉት ነገር ማድረግ ከሚገባቸው በታች እንደሆነ በማሰብ፤ ራሳቸውን ለችግር አጋልጠው ወንድሞችን ያገለግሉ ዘንድ፤ ከዐቅማቸው በላይም የሆነውንም እንኳ ወደው እንደሰጧቸው ሐዋሪያው ይመሰክርላቸዋል። ቅዱሳንን ለመርዳት ትብብር ሌላውን የሚለምኑ ሳይሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስን የሚለምኑ ናቸው። **(2** ቆሮ **8፡1-5)**

የመቄዶንያ ሰዎች ለመልካም *ሥራ* የሚለምኑ እንጂ የሚለመኑ አይደሉም። **2**ቆሮ **8፥6-7** ላይ የቆሮንቶስ ሰዎች ጥሩ የሚባል መንፈሳዊ ሁኔታዎቻቸውን ያነሳል።

- በእምነት
- በፍጹም ትጋት

- በቃል
- ለእኛ ባላችሁ ፍቅር
- በእውቀት

በእነዚህም ከሌሎች አብያተ ክርስቲያኖች የላቃችሁ እንደሆናችሁ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ በዚህ ቅዱሳንን በማገልገል ትሳተፉ ዘንድ ዐደራ እላችኋለሁ። **(**ቁጥር **9)**

ምሳሌ ሁለትን ደግሞ ተመልከቱ **:-**

***ii)*** *የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ተመልከቱ*

ከላይ የመቄዶንያ ሰዎች ሰላደረጉት ቸርነት ***ጸጋ*** ብሎ ጠርቷል። በዚህም አሁን ደግሞ፣ ጌታ ኢየሱስ ለእነርሱ ያደርገውን ነገር ያስቡ ዘንድ፤ ጳውሎስ ይህንን የጌታችንን ቸር ስጦታ *ጸጋ* በማለት ይጠራዋል። ይህንን ምንባብ አንዴ በሌላ ቅጇ ብንመለከት የተሻለ ገላጭ ነው።

***<u>2Cor 8:9 (NRSV)</u>***

***"For you know the generous act of our Lord Jesus Christ,***

***That though he was rich, yet for your sakes he became poor,***

***So that by his poverty you might become rich."***

አማኞች የሆኑትን ነገር ሁሉ የሆኑት፤ በክርስቶስ ከመሆናቸው የተነሳ ብቻ እና ብቻ ነው። ***"****እኛ የእግዚአብሔር ልጅ እንሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሄር ልጅ የሰው ልጅ ሆነ****"*** እንዲል ቅዱስ አትናቲዮስ። እርሱ ስለእኛ ብሎ የተዋረደው *ሥጋችንን* የለበሰውን፣ የጌታችንን ልግስና ስናስብ፤ ያለንን ነገር ለሌሎች ለማድረግ ልባችን እንዴት አይበረታታ**?**

ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲናገር**:-**

*<u>ፊልጵስዩስ **2** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*⁶ እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር*

*መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤*

*⁷ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤*

እነዚህ ሁለቱ ምንባባት የተጻፉት በአንዱ ሰው ነውና፣ ***"****ራሱን ባዶ አደረገ ሲልና፣ እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ፤ እርሱ ደሃ ሆነ****"*** የሚለው አገላለጽ በንፅፅር ልንረዳው የ**[**ሚ**]**ገባ ነው።

***"****እርሱ ዝቅ ብሎ እኛን ከፍ አድርጎናል፣ እርሱ ተሰድቦ እኛ ተባርከናል፣ እርሱ ተገርፎ እኛ ተፈውሰናል****"*** ታዲያ ይህ ሁሉ የሚያሳየን እርሱ **[**ኢየሱስ ክርስቶስ**]** እንዴት ያለ ቸር መሆኑን አይደለምን**?**

በዚህ ክፍለ**-**ምንባብ ባለጠጋነት የያዘው ትርጉም ቁሳዊ ነገር አለመሆኑ አውዱን ተከትሎ ላነበበ ሰው ግልጽ ነው። አይ የለም የምትሉ እናንተ የቃል እምነት ትምህርት ተከታዮች ታዲያ መጠየቅ አለባችሁ፡**-**

ጥያቄ፡**-**

**i)** ጳውሎስ እርዳታን የሚሰበስብላቸው በይሁዳ ያሉ ቅዱሳን ደሃዎች ተብለዋል **(**ገላ **2፥10)** ፤ ታዲያ ኢየሱስ በይሁዳ ላሉ ቅዱሳን አልሞተምን**?**

**ii)** የመቄዶንያ ሰዎችም ደሃዎች ናቸው **(2**ቆሮ **8፥2)** ፤ እነዚህን ጳውሎስ ለምን ***"confess"*** አድርጉ፣ ***"****እኔ ሐብታም ነኝ****"*** በሉ ለምን ሳይላቸው ቀረ**?** ደግሞስ እንዴት ደሃ ሊሆኑ ቻሉ**?**

**iii)** በዚህ አውድ የባለጠግነት ትርጉም ምንድነው**?**

**iv)** በአጠቃላይ ሁላችሁም የቃል እምነት ተከታዮች፤ በየመርሃ ግብራችሁ መግቢያ ላይ ታውጃላችሁ፤ አዋጃችሁ ደግሞ ***"****እኔ ባለጠጋ ነኝ፣ ክርስቶስ ለእኔ ሲል ደሃ ሆኗል፤ እኔ ባለጠጋ እሆን ዘንድ****"*** ነው። ታዲያ ይህ ሁሉ እውነት ቢሆን ጳውሎስ እየተዟዟረ ለምን

ለቤተ ክርስቲያን መዋጮን ይሰበስባል**?** ስለምንስ አንድ አፍታ እንኳ እነርሱ ጋር ሄዶ **confess** እንዲያደርጉ አላደረጋቸውም**?**

እነዚህን ጥያቄዎች ትመልሱ ዘንድ ግድ ይላችኋል**!!**

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ስድስት

### *“በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።”*

በአንድ አጋጣሚ አንድ ወንድሜ ሲናገር ***“****እግዚአብሔር የቃሉን ብርሃን ካላበራልህ፤ የሮሜን መጽሐፍ ከፍተህ የብልጽግና* ***‘****ወንጌል****’*** *ትሰብካለህ****”*** ሲል እንደሰማሁ አስታውሳለሁ። በጣም በሚያስደንቅ ሁኔታ የቃል እምነት መምህራን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን የሚመለከቱበት መንገድ ፍጹም ስሁት እና መጽሐፉ ሊናገር የፈለገውን ሳይሆን፤ እነርሱ**(**የቃል እምነት ተከታዮች**)** መጽሐፉ እንዲልላቸውን የሚፈልጉትን በማስባል ላይ የተመሠረተ የሥነ**-**አፈታት መርህ ነው የሚከተሉት። ሁለት ዓይነት የፍታቴ መንገዶች አሉ።

አንደኛው፡**-** ቅዱሳት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጽሐፍ ቅዱስን ሲጽፉልን፣ ሰዎቹን መንፈስ ቅዱስ ከስህተት ጠብቆ እና መጽሐፉንም ደግሞ በዘመናት ጠብቆ፣ በየዘመናቱ ለሚመጡት ሰዎች ሁሉ የሆነ የእርሱ መልዕክት አለው**(**መጽሓፍ ቅዱስ**)**። መልዕክቱ የአምላካችን እስከሆነ ድረስ በፍጹም ቅንነት የቃሉ ባለቤት እኛን ያስተምረን ዘንድ በእውነተኛ የሕይወት መስታወት ፊት ርቃናችንን በመሆን፣ እድፋችንን እንዲያሳየን በመለመን እና በቃሉ መንጻትን በመፈለግ የቃሉን ትርጉም ከእርሱ**(**ከቅዱስ ቃል**)** ወደ እኛ የምንፈልግበት መንገድ ነው።

ሁለተኛው፡**-** ደግሞ ከዚህ በተቃርኖ ያለ ነው። መጽሐፉ ሊናገር የፈለገውን ነገር ሳይሆን፤ የእኛ ስሜት የሚፈልገውን ያንን ብቻ ለመስማት ካለን ጉጉት የተነሳ የቃሉን ትርጉም እና የስነ**-**አተረጓጎም ስልትን በጥንቃቄ ሳንፈትሽ፤ በመስታወት ፊት ቆሻሻውን ደብቆ ጥሩውን ብቻ ያይ ዘንድ የሚፈልጉትን ዓይነት፣ እግዚአብሔር ሊናገር የፈለገውን ሳይሆን እኛ መስማት የፈለግነውን ብቻ ምንፈልግበት እና የምንሰማበት መንገድ ነው።

ብስራት ብዙአየሁ(ጃፒ) *"እምነት"* በሚል ርዕስ በተከታታይ ሲያስተምር፤ በሁለተኛው ክፍል ላይ በዙሪያችን ያለንን እውነታ ስለመካድ እና ይህም በእነርሱ አጠራር *"እምነት"* ተብሎ እንደሚጠራ ያስተምራል። በእርግጥ እምነት ምንድነው**?** ለሚለው ራሱን ያቻለ ክፍለ ጊዜ አዘጋጅቼ የማስተምር ይሆናል፡፡ አሁን ግን በአጭሩ ብስራት ብዙአየሁ**(**ጃፒ**)** የተናገረውን ላቅርብ፡**-** ብዙ ችግር እና ብዙ ሕመም ከገጠማችሁ እንዲህ በሉ *"ከአሸናፊዎች እበልጣለሁ"* እንጂ ሁኔታችሁን አትመልከቱ በማለት አስተማረ።

ይህንን ምንባብ ጃፒ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ታምራት ታረቀኝ **(cj)** ፣ ተዘራ ያሬድ፣ ዳንኤል ጌታቸው **. . .** ወዘተ የቃል እምነት መምህራን የሚረዱት እንዲሁ ነው።

እስቲ የቃሉን ምንባብ ትርጉም እንመልከትና ጥያቄዎችንም ላቅርብ፡**-**

***<u>ሮሜ 8፥37 (አዲሱ መ.ት)</u>***

*"ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።"*

ይህ ምንባብ ከላይም ከታችም ምንም የሌለው ቢሆንና፤ የሮሜ መልዕክት ይህ ብቻ ቢሆን ብላችሁ አስቡና ከዚህ ዓረፍተ ነገር ምንድነው ልትረዱ የምትችሉት**?** ሦስት ነገሮችን ነው አይደል**?**

**i)** በሆነ አካል ተወደናል **[**በእርሱ**]**

**ii)** በእርሱ ደግሞ አሸናፊ ተብለው የሚጠሩ አሉ፤ ቢሆንም በእርሱ አሸናፊዎችንም እናሸንፋለን

**iii)** ከእርሱ ሊለየን አይችልም

የሚሉ ሦስት ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን ጳውሎስ አሸናፊ የተባሉትም ዘርዝሮልናል እስቲ የተወሰነ ከፍ እንቅ ዝቅ ብለን እንመልከት፡**-**

***<u>ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት)</u>***

*31 ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን**?** እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል**?***

*32 ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣*

*ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን**?***

*33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው**?** የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤*

*34 ታዲያ የሚኰንን ማን ነው**?** የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣*

*በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል።*

*35 ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው**?** ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣*

*ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ**?***

*36 ይህም፣ **“**ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፤*

*እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን**”** ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።*

*37 ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።*

*38 ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣*

*ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣*

*39 ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም ፍጥረት፣*

*በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።*

***“**የሁሉ ዳኛ እና ጌታ እግዚአብሔር ከእኛ ነው ታዲያ ማን ሊቃወመን **(**ሊፈርድብን**)** ይችላል**”*** በማለት እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ ይመስሉ ዘንድ፣ የወሰናቸው **(8፥28-29)** ፣ ያጸደቃቸው እና ያከበራቸውን እነርሱን ወደር የሌለው ፍቅሩን አንድ እና ብቸኛ ልጁ ሳይሳሳ የሰጠላቸውን **(**ቁጥር **32)** እነርሱን የሚቃወም ማን ነው**?**

የሚያጸድቅ እርሱ ነው፤ እርሱ አጽድቋቸዋል ታዲያ የሚኮንናቸው ማን ነው**?** እግዚአብሔር አብ ከእኛ ጋር ነው፤ ስለዚህ ማንም አይቃወመንም ይላል ጳውሎስ **(8፥33)** ።

ስለእነዚህ የእግዚአብሔር ምርጦች ወልድ ከሙታን በመነሳት አሁን በሰማይቷ ድንኳን ስለ እነርሱ ይታያል **(**ይማልዳል**)**። ታዲያ ከእግዚአብሔር ፍቅር ማን ሊለየን ይችላል፤ እግዚአብሔር በልጁ በኩል አሁንም እየተመለከተ ካለ**?** እግዚአብሔር ወልድም ከእኛ ጋር ነውና ማንም ከክርስቶስ ፍቅር አይለየንም**!! (**አሜን**)**።

ጳውሎስ ***"****እግዚአብሔር አብ በወልድ በኩል ተቀብሎናን ስለዚህ ምንም አይነት ነገር ከሰማይ በሆነ ነገር አየለየንም****"*** ይለንና፤ በምድር ሰዎችን ከእግዚአብሔር አብ ፍቅር እና ከክርስቶስ ፍቅር ሊለይ ይችላሉ ስለሚባሉ ነገሮች ይዘረዝራል። እስቲ እንቁጠራቸው፡**-**

1. መከራ
2. ጭንቀት
3. ስደት
4. ራብ
5. ራቁትነት
6. ፍርሃት
7. ሰይፍ
8. ሞት
9. ሕይወት
10. መላዕክት
11. ግዛት
12. ያለውም ቢሆን
13. የሚመጣው **(**ገና ያልመጣው**)**

እነዚህን ሁሉ ሐዋሪያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ ይለናል።

አማኝ መከራ ሊገጥመው ይችላል፣ አማኝ በሚደርስበት ነገር ሊጨነቅ ይችላል፣ ስደትም ሊመጣ ይችላል፣ ረሃብ ሊገጥመው ይችላል፣ በገንዝብም ዕጦት ራቁት ሊሆን ይችላል፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ከባድ ፍርሃት

ውስጥ ሊገባም ይችላል። እነዚህ ምንባባት ሁሉ የሚያሳዩን ነገር ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

***2ኛ ቆሮንቶስ 11 (አዲሱ መ.ት)***

*24 አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል።*

*25 ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤*

*ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤*

*26 ብዙ ጊዜ በጕዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣*

*ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣*

*ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር።*

*27 ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤*

*ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቍትነት ተቈራምጃለሁ።*

*28 ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው።*

ይህንን ነው ጳውሎስ ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን የሚለው፤ በምድር ስለሚገጥመው መከራ መናገሩ ነው። ***(ሮሜ 8፥36)***

ስለዚህ ይህ ምንባብ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ሲል ***"ማሸነፍ ከእግዚአብሔር ፍቅር አይበልጥብንም"*** ማለቱ እንጂ፤ ***"በሽታ አይዘንም፣ ደሃ ልሆን አልችልም፣ መከራ አይገጥመኝም"*** ማለቱ አይደለም። አይ የለም ይህንን ክፍል የምረዳው አሸናፊ መሆን ሲል አለመታመም እና ባለጠጋ መሆን ነው ለምትሉ ከሆነ እንካችሁ ተጠየቁ፡-

## ጥያቄ፡-

**i)** በዚህ ምንባብ አሸናፊ መሆን ምን ማለት ነው**?**

**ii)** በዚህ ምንባብ ጳውሎስ የዘረዘራቸውን ነገር ከተናገረ ወዲያ ***"በዚህ ሁሉ ግን"*** ሲል ምን ማለቱ ነው**?**

**iii)** ቢያንስ ጳውሎስ ይህንን መልዕክት አንተ እንዳልከው እያለ ከሆነ **(**እንበልና**)** በ**2**ኛ ቆሮ ጳውሎስ ተርቤያለሁ ተጠምቻለሁ ይላል እና መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በራሱ ይጣረሳልን**?**

**Iv)** ጳውሎስ መጨነቁን ተናግሯል፤ ታዲያ አንተ ደግሞ አልጨነቅም ብለህ በማወጅ ከጭንቀት ነጻ መውጣት አለብኝ ትላለህ፣ ይህንን ከጳውሎስ ሕይወት የምንማረው ነው ወይ**?**

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ሰባት

### *"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።"*

***"ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በስጋ ውስጥ ያድራል!"*** ከሚለው የቃል እምነት ኑፋቄ ዳሰዳ እስከ አሁን ያለውን**(**የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ**)** እየተከታተላችሁ ከሆነ የስህተታቸውን ምንጭ በቀላሉ የተረዳችሁ ይመስለኛል። **"**አውድ**!** አውድ ንጉስ ነው**!"** የአንድን ጽሁፍ ከአውዱ አፋትቶ መረዳት፤ ከእውድ ስንጣላ በቀላሉ ጸሐፊው ሊነግረን የፈለገውን ነገር ትተን ራሳችን ማለት የፈለግነውን ወይም መስማት የፈለግነውን ነገር ያንኑ እንደ ገደል ማሚቶ ከልባችን ወጥቶ በጆሮአችን የሚደመጥ ይሆናል።

የቃል እምነት ኑፋቄ መምህራን ትልቁ በሽታቸው ይኸው ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሊል የፈለገውን አውዱን በጠበቀ መንገድ መፍታት ሳይሆን ***"ተገለጠልን፣ መንፈስ ነገረን"*** በሚል ከንቱ ተረት ከኬኔት ሔገን መጽሐፎች አንብበው ያመጧቸው ተራ የሰው ሐሳቦች ናቸው፣ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታቸው ሲፈተሽ የሚታይ መሆኑ ነው።

ለዚህ ማሳያ ደግሞ ዛሬ የፊል **4፥13** ላይ ያለውን እንመለከታለን፡**-**

ብስራት ብዙአየሁ **(**ጃፒ**)** ስለ እምነት ሲያስተምር ደጋግሞ ከሚናገራቸው ነገሮች ውስጥ ***"እምነት ምላሳም ናት"*** አንዷ ነች። ለምሳሌ የሕመም ስሜት ሲሰማኝ ***"በመገረፉ ቁስል ተፈውሻለሁ"*** ይላል እንጂ ታምሚያለሁ አይልም። ነገር ግን ጃፒም ሆነ በዚህ ተርታ የሚሰለፉ የቃል እምነት ኑፋቄ አስተማሪዎች ተዘራ ያሬድ፣ ታምራት ታረቀኝ፣ ሐይሉ ዮሐንስ **. . .** ወዘተ ልብ ማለት ያለባቸው ነገር የመልዕክቱ ደራሲ ለቀዳማይ ተደራሲያን ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ይህ ነው**?**፣ ይህ ይሁን አይሁን እንዴት ማወቅ ይቻላል**?** ጳውሎስ አሁን በሕይወት የለምና ***"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ"*** ማለትህ ምን ማለት ነው ብለን መጠየቅ አይቻለንም ታዲያ ምን ተሻለን**?**

አንዳንዶች ***"ይህንን ምንባብ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ገልጦልኛልና እንዲህ ማለት ነው"*** እስከማለት የደፈሩ፣ ደፋሮች ናቸው**!**፤ ዘላለም ጌታቸው በአንድ አጋጣሚ ይህንን ብሎ ነበር። የአንድ ቃል ትርጉም ቃሉ በሚገኝበት አረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል። ይህ ካልሆነ በአንድቀጹ ውስጥ እንደሱም ሆኖ ከከበደን፣ በመጽሐፉ ውስጥ ይህም ሆኖ አስቸጋሪ ሁኔታ ከሆነብን፤ ትርጉሙን ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ አንጻር መልዕክቱን እንወስናለን።

እስቲ ምንባብን ዳሰሳ ወደ ማድረግ እንግባ፡**-**

*<u>ፊልጵስዩስ **4** (አዲሱ መ**.**ት)</u>*

*[13] ኃይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ።*

እንደው እንበልና ይህ ምንባብ ለብቻው የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ነው እንበል፤ ከፍ ብለንም ሆነ ዝቅ ብለን ምንም አይነት ነገር የማናገኝ ቢሆን ብለን እናስብና እንዴት ያለ ትርጉን ይሰጠን ይሆን**?**

በሚያሳዝን ሁኔታ የቃል እምነት ኑፋቄ መምህራንም ከፍ ብሎ እና ዝቅ ብሎ የተባለ ነገር የሌለ ይመስል ይህንን ክፍል እንዲህ በማለት ይተረጉሙታል፡**-**

እግዚአብሔር ኃይልን ይሰጠኛል፤ እርሱ በሚሰጠኝ ኃይል **ሁሉን እችላለሁ** በማለት በአንድ ጊዜ ከሰውነት መደብ ወደ መለኮት መደብ ይሸጋገራሉ፣ ምዕመኑንም ያሻግራሉ። ሁሉን መቻል፣ በእነርሱ ትርጉም ሁሉን መቻል ነው፤ በቃ ምንም የማይችሉት ነገር የለም።

እስቲ **ሁሉን መቻል** በዚህ ምንባብ የተሸከመውን ትርጉም እንመልከት፡**-**

*<u>ፊልጵስዩስ **4** (አዲሱ መ**.**ት)</u>*

*[10] ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ መንፈስ ስለ እኔ ማሰብ በመጀመራችሁ፣*

*በጌታ እጅግ ደስ ይለኛል፤ በርግጥ በተግባር*

*ለመግለጽ ዕድሉ አልነበራችሁም እንጂ ማሰቡንስ ታስቡልኝ ነበር።*

*[11] ይህን የምለው ስለቸገረኝ አይደለም፤*

*ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን፣*

*¹² ማጣትን ዐውቀዋለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ። ብጠግብም ሆነ ብራብም፣*

*ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሆነ በየትኛውም*

*ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ።*

*¹³ ኀይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ።*

*¹⁴ ሆኖም የመከራዬ ተካፋይ ስለ ሆናችሁ መልካም አድርጋችኋል።*

ይኼ ክፍለ-ምንባብ እንደሚያሳየን ከሆነ የፊልጵስዩስ ሰዎች ስለ ጳውሎስ ተጨንቀዋል **(**ቁጥር **10)**፤ ይህ ጭንቀታቸውን ጳውሎስ ተረድቷል። በእርግጥ በአካል ቢሆን ደግሞ ምናልባት ይህንን ለጳውሎስ ያላቸውን መልካም ሐሳብ ከጳውሎስ ጎን በአገልግሎቱ በመቆም ያሳዩት ነበር፣ ነገር ግን ይህ አልሆነም። ምክንያቱም ጳውሎስ እርስ ቤት ነውና። ጳውሎስ ይህንን ሲል ለእነርሱ ሌላ ጭንቀት ላለመፍጠር በመጠንቀቅ ***"ይህንን የምለው ስለ ተጨነኩ አይደለም"*** ይላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመምሰል እና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት ቁልፍ የሆነውን ***"ያለኝ ይበቃኛል"*** በማለት የሚኖር እንደሆነ እንጂ፤ እንደሚቸገር አይናገርም። የፊልጵስዩስ ሰዎች ጭንቀታቸው የሚያስፈልገውን ነገር ባለማድረጋቸው ቢሆንም፣ ጳውሎስ ግን ያ ያለኝ እርሱ የሚበቃኝ ስለሆነ አትጨነቁ ይላቸዋል።

ይህ ማለት ደግሞ ምንም የጎደለኝ ነገር የለም ማለቱም አይደለም። ጳውሎስ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን እንዴት እንደተማረ ሲያስረዳ፡-

- ማጣትን አውቃለሁ
- ማግኘትንም አውቃለሁ
- መጥገብንም አውቃለሁ
- መራብንም አውቃለሁ

***"በእነዚህ ነገሮች መሃል ግን ባለኝ ነገር ደስተኛ ሕይወትን መኖር ለምጃለሁ፤ ስለዚህ አትጨነቁ።"*** ይላቸዋል በብዙ ድካሙ ሊቆሙለት የፈለጉ የፊልጵስዩስ ወዳጆቹን።

እነዚህ ነገሮች ጳውሎስን ከወንጌል አገልግሎት ሆነ፣ ለጌታ ኢየሱስ ካለው ፍቅር ሊለዩት ይችሉ ይሆን**?** ብለው ተጨንቀዋል። ይህ አይነት ጭንቀት እና ማጣት ስጋዊ በሆነ ልምምድ ብቻ የሚቻል አይደለም። ክርስቲያን መከራ እንደማያገኘው አይናገርም፤ ይልቅ በመከራው ውስጥ ግን ጌታ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል።

ብዙ ሰዎች በመከራ ውስጥ ማለፍ አልቻሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ኢየሱስ ከተናገረው ምሳሌ ውስጥ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ ስለ መልካሙ መሬት እና ስለጭንጫ መረት ምሳሌ እንመለከታለን። በጭንጫ መሬት ላይ የወደቀው ዘር ወዲያ በቅሎ ነበር ይሁን እንጂ ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ጸሐይ በወጣ ጊዜ ወዲያው ጠወለገ፤ እነዚህም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይስ ስደት ሲመጣ ወዲያው የሚሰናከሉት ናቸው።

ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው በተዓምር ይመግባቸው ዘንድ ሲጠብቁ፣ ይህንን ባለማድረጉ እርሱን ከመከተል ወደኋላ ብለዋል። ጳውሎስ በዚህ ሁሉ መከራ ማግኘት ማጣት ስቃይ ውስጥ አንድን ነገር ተማምኗል ይህም፡**-**

***"ኃይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን እችላለሁ"*** የሚል ነው። ተስፋው ኃይልን በሚሰጠው በእርሱ በጌታው እንጂ በራሱ እምነት ወይንም **confession (**ቃል ማውጣት ወይም ማወጅ**)** አይደለም።

ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ ሁሉን እችላለሁ ሲል ከዚህ የከፋም መከራ እና ስቃይ ቢመጣም እነርሱንም እችላለሁ ማለቱ ነው፤ በአውዱ ስንመለከት።

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ስምንት

### *የቃል እምነት አስተምህሮ በእምነት አባቶች ሕይወት ሲዳኝ*

በዚህ ክፍል ልንመለከት ያለው አጠቃላይ የቃል እምነት መምህራን ስለ መለኮታዊ ፈውስ ሆነ መለኮታዊ ብልጽግና ያስተማሩትን፣ ከእምነት አባቶች ግለ ታሪክ ጋር በማመሳከር ትምህርታቸው በእምነት አባቶች ሕይወት የተረጋገጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን እናያለን።

እነዚህ የእምነት አባቶች በዕብራዊያን መጽሐፍ ምዕራፍ አስራ አንድ ያሉ ቢሆኑም፣ እኔ ግን የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ዋቢ አድርጌ አቀርባለሁ። ከሁሉ አስቀድሜ አንድ ጥያቄ ልመልስ። አንባቢዬ ሆይ ይህንን ለምን እንደማደርግ ግልጽ ላደርግ ነው፤ ክርስትና የምናወራው ብቻ ሳይሆን እውነትነቱ በሕይወታችንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚገለጥ ነው። በዚህም መሠረት ከአስተምህሮ ሕይወት ይቀዳል። ለምሳሌ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ዝም ብለን የምናወራው ነገር አይደለም፣ ይልቅ መጽሐፍ እንደሚል፡-

<u>*ሮሜ **5፡5** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤*

*እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና።"*

ስለዚህ ለምናወራው ለዚያ ነገር ምስክሮች እንጂ እንግዶች አይደለንም። ምስክር መስካሪ ነው፤ ምስክርነቱ ስላየው እና ስለሰማው ነገር በእርግጠኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለ እግዚአብሔር ፍቅርም እንዲሁ ነው። ስለ ቸርነት፣ ትዕግስት፣ ጽናት . . . ወዘተ የመሳሰሉት የክርስትና አስተምህሮ ማጠንጠኛዎች፣ በአማኞች ሕይወት የሚገለጥ ነው።

ስለዚህ የቃል እምነት መምህራን ***"I am unstopable, I am a winner"*** ምናምን ሲሉ ይህ ንግግራቸው በእምነት አባቶችም የተገለጠ ሊሆን ይገባል፤ እንጂ ጳውሎስ እና ጴጥሮስ ዛሬ ቢመጡ የሚደነግጡበት እንግዳ ልምምድ መሆን የለበትም፤ ነገር ግን ይህ ልምምድ ለጳውሎስ እና ለጴጥሮስ እንግዳ ነው። አንዱን መንፈስ ከተቀበልን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል**?** እነርሱ ደካሞች ነበሩ**?** አንዳንድ የእምነት ቃል መምህራን ደፋሮች እና ተሳዳቢዎች ናቸው። *አዎ* ለማለት አያፍሩም፤ ነገር ግን ሁሉም በአንድነት እንዴት ይህንን አይነት ነገር አያውቁም/አያስተውሉም**?**

የቃል እምነት መምህር የሆነው ብስራት ብዙአየሁ **(**ጃፒ**)** ስለ እምነት ሲያስተምር ***"****ቃሉን በትክክል የማያስተምሩ ሰዎች ነቢዩ ኤልሳዕ ሊሞት ባለው በሽታ ታሞ****"*** የሚለውን ጠቅሰው ***"****በቃ ልሞት ነው ይላሉ****"*** በማለት ተቃዋሚዎቹ ላይ ሊሳለቅ ሞክሯል ጃፒ በዚህ ብቻ አላበቃም፤ ***"****መለኮታዊ ፈውስ ለእኛ የእግዚአብሔር ፈቃድ****"*** በሚል ርዕስ ሲያስተምር ***"****የሞተባችሁ ሰው ካለ እግዚአብሔር ጠራው አትበሉ እግዚአብሔር አይጠራም****"*** በማለት እግዚአብሔር ሳይሆን ሰይጣን ሰዎችን እንደሚገድል አስተምሯል። በዚህ ሃሳብ ላይ በቀጣይ ክፍል በሰፊው እመለሳለሁ ነገር ግን ዋናው የዛሬው ነጥቤ ***"****አንታመም፣ ባለጸጎች ነን****"*** የሚለው የቃል እምነት ትምህርት በእምነት አባቶች ሕይወት የተገለጠ ነው**?** ወይስ እነርሱ ብቻ የሚያውቁት እና የሚያስተምሩት**?** የሚለው ማየት ነው። እስቲ በአይሁድ ሆነ በክርስቲያኑ የሐይማኖት አባት በመባል የሚታወቀው አብርሃምን እንመልከት፡**-**

አብርሃም ልክ እንደ እኛ ያለ አማኝ ነው። አብርሃም የጸደቀው በእምነት ነው **(**ሮሜ **4**፥**1-3)** ፤ እግዚአብሔር ራሱ ለአብርሃም ወንጌልን ሰበከለት። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ስለ አብርሃም ይናገራል። ግለ**-**ታሪኩ በሰፊው የሚገኘው ደግሞ ወደ ዕብራዊያን በተጻፈው መልዕክት ነው። አጻጻፉ ግለ**-**ታሪኩን በማቅረብ ይመስላል።

አብርሃም እግዚአብሔር እንደሚሰጠው በማመን ወደ ተናገረው *ሥፍራ* ይወጣ ዘንድ ሲያዘው በእምነት ታዘዘ **(**ዕብ **11**፥**8)** ይህንን ሃገር ቢወርስ እንኳን አኗኗሩ እንዴት እንደሆነ ጸሓፊው ሲናገር እንዲህ ብሎ ነው፡**-**

*ዕብራውያን **11** (አዲሱ መ.ት)*

*⁹ በባዕድ አገር እንዳለ **መጻተኛ በተስፋዪቱ** ምድር በእምነት ተቀመጠ፤*

*የተስፋውን ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ፤*

*¹⁰ ምክንያቱም **መሠረት** ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር።*

አብርሃም የኑሮ ዘይቤው የቃል እምነት እንደሚሉት አይነት አይደለም፤ ይልቅ በተቃርኖ የሚኖር ነው። ምክንያቱም አብርሃም ***"ወረስኩ"*** እና ***"የእኔ ነው"*** እያለ ያየውን ሁሉ የሚመኝ ሳይሆን፤ ይልቅ እግዚአብሔር የተናገረውን ያንን የተስፋ ቃል አግኝቶ እንኳን በዛ ምድር ላይ ኑሮው እንደ መጻተኛ ነው። አብርሃም የምድር ላይ ኑሮው ዘላለማዊ እንዳልሆነ ተረድቷል፤ ዘላለማዊ የሆነችውን ያቺን የእግዚአብሔርን መንግስት የሚጠብቅ ነበር። ከአብርሃም ሕይወት ልንማረው የምንችለው ትልቅ ነገር ምን መሆን አለበት**?** ስለ ገንዘብ እና ምድራዊ ነገር ምን ትምህርት ይሰጠናል**?**

ሌላኛው ደግሞ ግለ-ታሪኩን እናይ ዘንድ የመረጥኩት ሙሴ ነው፤ ሙሴ በንጉስ ቤት ያደገ ነው፣ ችግር መከራ እና ስቃይ ሳያውቅ ነው። ሙሴ ያደገው በቃል እምነት መምህራን አባባል ከሆነ ***"I am winner"*** ማለት ሳይጠበቅበት ግን በምድራዊ አባባል ምቾት ያለው ኑሮ የሚኖር ነው። ነገር ግን ሙሴ ለንግስና ሲጠበቅ ድንገት እምቢኝ አለ **(**ዕብ **11፥24)** ይህንን ንግስና ለምን እንዳልፈለገ መጽሐፍ ሲናገር እንዲህ ይላል

*ዕብራውያን **11፥26** (አዲሱ መ.ት)*

*"ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ*

*ሀብት መሆኑን ተገነዘበ፤ ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶአልና።"*

ታዲያ የሙሴ ስለ ምድራዊ ሐብት እና ብልጽግና ምን አይነት አመለካከት ያለው ይመስላችኋል**?** ሙሴ ምድራዊው ነገር ማጣት ሆነ ማግኘት ከንቱ መሆኑን ተረድቷል፤ ይልቅ ጊዜያዊ በሆነ በዚህ ምድር ሳለ ዘላለማዊውን የሆነውን ክርስቶስን ተመልክቶ ልክ እንደ እኛ ስለ ክርስቶስ በዚህ ምድር መከራን

መቀበልን መረጠ። ለሙሴ ብልጽግና ምንድነው? ብትሉ መልሱ ከክርስቶስ ሕዝብ ጋር ስለ ክርስቶስ ብሎ መከራን መቀበል እንጂ ምድራዊውን ግሳንግስ ማግኘት አይደለም። ቢሆንማ ኖሮ ሙሴ ስለምን ንግስናውን እምቢኝ ይላል?

ሌላኛው ግለ-ታሪክ የአዲስ ኪዳን አብዛኛውን መጽሐፍ የጻፈው ሐዋርያ ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ አስቀድሞ ይሁዲ የነበረ ሲሆን ከደማስቆ ጉዞ በፊት ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ እና አማኞችን የሚያሳስር ሰው/ግለሰብ ነበር። በጊዜው በነበረው ሁኔታ ጳውሎስ ታላቅ የሕግ መምህር ነበር በዚህም ኑሮው እጅግ ጥሩ እና በጊዜው ከነበሩ መካከል ከበርቴዎች ሰዎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው። ይህንን ሰው ጌታ በደማስቆ መንገድ ላይ ክርስቶያኖች ያስር ዘንድ ፈቃድ ወስዶ ሲሄድ ነው ያገኘው፣ ይህም በሕይወቱ ታላቁን የጌታን ኃይል የተመለከተበት ነው (ሐዋ 9፥1 )። ይህ ሰው ከዚህ በኋላ ሕይወቱን ሁሉ የኖረው ይህንን ታላቅ የጌታን ኃይል በመመስከር ነበር። ኑሮውንም ድንኳን በመስፋት ላይ ያደረገ ታላቅ ሰው ነው። ምንም እንኳ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ከቤተ-ክርስቲያኒቱ ቀለብን ያገኙ ዘንድ ቢገባም፤ ጳውሎስ ግን ባለው ነገር ሁሉ የሚያገለግል እንጂ የሚቀበል አልነበረም። ይህ ሰው ብዙ አይነት ነገር አሳልፏል የራሱን ምስክርነት ቃል በቃል እንመልከት፡-

<u>*ፊልጵስዩስ 4፥12 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*“ማጣትን ዐውቀዋለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ።*

*ብጠግብም ሆነ ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሆነ*

*በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ።”*

ጳውሎስ ተቸግሮ የማያውቅ አይደለም ፈልጎም ያጣው ነገር ነበር፣ ተርቦም ነበር፣ ጠግቦም ነበር፤ ይህ ምንም አያስደንቅም። ነገር ግን የቃል እምነት መምህራን እንደሚሉት አይደለም ሕይወቱ። ምድራዊ ተድላን ንቆ ጌታን ለተከተለ ሰው ማጣት ምኑ ነው? ጳውሎስ ምን እንደሆነ በማይታወቅ በሽታ ይቸገር እንደነበር ራሱ ይናገራል።

*<u>ገላትያ **4፥14** (አዲሱ መ.ት)</u>*

***“**ሕመሜ ለእናንተ ፈተና ሆኖባችሁም እንኳ፣*

*አልሰለቻችሁኝም፤ ወይም አልተጸየፋችሁኝም**”***

መታመም ብቻ ሳይሆን በጣም የሚታይ እና ምናልባት እርዳታ የሚያስፈልገው ሁኔታ ውስጥም ነበር ማለት እንችላለን። ታዲያ ጳውሎስ ክርስቲያን አልነበረም ወይ**?** ምናልባት ይህንን በሽታ የገመትን እንደሆን ቀጥሎ ባለው ምንባብ ዓይናችሁን እንኳን አውጥታችሁ ብትሰጡኝ ብሏልና፤ ዓይኑ በጣም የታመመ የሚያልቅስ ወይስ የሞጨሞጨ አይን ለማየት ደስ የማይል ቢሆንም የገላቲያ ሰዎች አልተጸየፉትም። የቃል እምነት ትምህርት ጳውሎስ ሕይወት ውስጥ የሌለ ነው፤ ይልቅ ጳውሎስ ገንዘብ አጥቶም ያውቃል በደዌም ክፉኛ ተመቶ የሚያውቅ ሰው ነው።

*<u>**2**ኛ ቆሮንቶስ **12** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*⁷ ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታ በይ የሥጋዬ መውጊያ፣*

*እርሱም የሚያሠቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ።*

*⁸ ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤*

ከላይ እንዳልኳችሁ የእምነት አባቶች አስቀድመው በክርስቶስ ሳይሆኑ ነበር ኑሯቸው በምድራዊ ነገር የተባረኩ የነበሩ ናቸው። ነገር ግን በሕይወታቸው የገጠመው ነገር ክርስቲያን ስለሆኑ፣ የበለጸጉ እና ገንዘብ ያላቸው መሆን አልነበረም፤ ይህን የቃል እምነት ልምምድን ከቶ አያውቁትም።

ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ የሆነው በኤፌሶን ቤተ**-**ክርስቲያን መጋቢ ጢሞቲዮስ በሆድ በሽታ ሲቸገር ተመልክቶ፤ እንዲህ በማለት መክሮታል፡**-**

*<u>**1**ኛ ጢሞቴዎስ **5፥23** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*“ለሆድህና ደጋግሞ ለሚነሣብህ ሕመም፣*

*ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት እንጂ ከእንግዲህ ውሃ ብቻ አትጠጣ።”*

ማጠቃለያ፡-

የቃል እምነት መምህራን አስተምህሮ አንደኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች ሕይወት ጋር የማይመሳከር ነው። ይህ ምንን ያሳየናል**?** ይህ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ትምህርታቸው የተቀዳው ከመጽሐፍ ቅዱስ አለመሆኑን፤ እና ልምምዳቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቃርኖ ያለ ትምህርት መሆኑን ነው።

# የሐብት እና የብልጽግና "ወንጌል" ኑፋቄ ዳሰሳ

## ክፍል ዘጠኝ

### *ማጠቃለያ፡-*

### *ስለ በሽታ እና ድኽነት ምን ልናውቅ ይገባል?*

ያለፈው ክፍል ላይ**(**በክፍል ዘጠኝ**)** የተለያዩ የእምነት አባቶችን ተመልክተናል አብርሃም፣ ሙሴ፣ ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስ በተለያየ ዓይነት ሁኔታ በምድር የነበሩበትን ሁኔታ አይተናል፤ አኗኗራቸው በምን መንገድ ለእኛ ትምህርት እንደሚሆነን ቃኝተንም ነበር።

በዚህ ክፍል ደግሞ የእስካሁኑ ማጠቃለያ የምንሰጥ ይሆናል። በእርግጥ አንድ የቃል እምነት አስተማሪ፣ ተከታይ *"ጳውሎስ ታሞ ነበር ታዲያ እኛ እንታመማለን ማለት ስህተት ነው"* ይል ይሆናል። እኔ ያለፉት ክፍሎች ውስጥ ይህ የቃል እምነት ከንቱ ተስፋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው እና በእምነት አባቶች ሕይወት ያልታየ *ባዕድ ነው* ማለቴ እንጂ ስለ በሽታ ልናስብ የሚገባን መሠረታዊው ነገር ሌላ ነው። አንታመም የሚለው ትምህርት እውነት ቢሆን ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ደጋግሞ ስለ ስለ አማኞች የድነት ዋስትና **(Assurance of Belivers Salvation)** ሲናገር በተቃራኒ አንድም ጊዜ እንኳን በማመናችን ምክንያት በሽታ እና ድህነት እንደማይጠጋን ተስፋን አለመስጠቱ ነው።

ታዲያ ስለ በሽታ ምን ማሰብ አለብን**?**

***i)*** *በሽታ እግዚአብሔርን ያገለግላል*

*"አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ዘላለማዊ የኃይሉን ክብር፥ የኃይሉን ጥበብ ፤ የኃይሉን መልካምነት ለመግለጽ የሚታዩትን የማይታዩትን በስድስት ቀን በመጀመሪያ ለመፍጠር መልካም ፈቃዱ ሆነ። የፈጠረውም ሁሉ መልካም ነበር።"*

***The westminister confession of faith*** *ምዕራፍ አራት ቁጥር አንድ*

ስለዚህ አስቀድሞ ሰው ሲፈጠር የእግዚአብሔርን ታላቅ እና ድንቅ ጥበቡን የሚያሳይ ሆኖ ነበር። ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በሰይጣን ተንኮለኛ ፈተናና አታላይነት የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ በመብላት ኃጢአት ሰሩ። ይህ የሁሉ ነገር ጅማሮ ነው፤ ከዚህ በመቀጠል ሰው በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ ምክንያት ምን እንደሆነ ጳውሎስ በግልጽ ይናገራል።

*ሮሜ **5፣12** (አዲሱ መ.ት)*

*“ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣*

***ሞትም** በኀጢአት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤*

*ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤”*

ሞት በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት መንገድ ተግልጿል፡-

1. *ስጋዊ ሞት፡-* ይህ ሞት ነፍስ ከስጋ ተለይታ ወደ ፈጣሪዋ የምትሄድበት ነው። ይህም አንደኛው በኃጢአት ምክንያት የተከሰተ ነው።
2. *መንፈሳዊ ሞት፡-* ከቃሉ እንደምንረዳው ይህ ሞት መንፈሳዊ ግንኙነትን አመላካች ነው። ይህ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ክብር በመጉደሉ የተነሳ ያጣውን መንፈሳዊ ሕብረትን ያመለክታል። ይህም ሌላኛው የኃጢአት ውጤት ነው።

***3.*** *ዘላለማዊ ሞት፡-* ዘላለማዊ ሞት ደግሞ በፍርድ ዕለት የሚሆን ሲሆን ይህም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያላመኑ ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች የሚሆኑበት ነው። ይህም የኃጢአት ውጤት ነው።

በምንም ይሁን በምን ሁላችንም እንሞታለን። አንዳንዶቻችን ልንሞት ያለው በበሽታ ሊሆንም ይችላል። ታዲያ ይህ እኛ አማኞች ከኃጢአተኛ እና እግዚአብሔርን ከማያከብር ሕይወት ፍጹም ወደ ሆነው ወደ ልጁ መንግስት የምንገባበት ድልድይ ነው፤ በዚህም በሽታ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው።

***ii)*** *በሽታ በጌታችን ላይ ያለንን መታመን ማረጋገጫም ሊሆን ይችላል*

መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ከተመዘገቡ ድንቅ ግለ ታሪኮች ውስጥ በጣም የሚያስገርመኝ የኢዮብ ግለ-ታሪክ ነው። ኢዮብ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፋት የራቀ (ኢዮብ **1፥1**) ቢሆንም እግዚአብሔር ኢዮብን ይፈትነው ዘንድ ለሰይጣን አሳልፎ ሰጠው። ሰይጣን ወደ እግዚአብሔር በመምጣት ***"****የኢዮብ ባንተ መታመን ባለው ንብረት የተመሠረተ እንጂ ፍጹም አይደለም****"*** አለው።

<u>*ኢዮብ **1፥11** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"እስቲ፣ እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ንካበት፤*

*በእርግጥ ፊት ለፊት ይረግምሃል።"*

በዚህም እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ መከራ እና በሽታ ይመጣ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፎ ሰጠ። ይህ አይነት ፈተና በሕይወታችን ሊያመጣ ስላለው ነገር ወይም ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

<u>*ሮሜ **5፥3** (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤*

*ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን።"*

በዚህ እግዚአብሔር ፈቅዶ በሕይወታችን በሚያመጣው ፈተና ወድቀን አንቀርም። ይህንን ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በጻፈው መልዕክቱ በግልጽ ተናግሯል፡-

***1ኛ ቆሮንቶስ 10፡13 (አዲሱ መ.ት)***

*“በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤*

*እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ*

*እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን*

*መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።”*

ከዚህ የተነሳ ኢዮብ እስከ መጨረሻው በመጽናት ሕይወቱ ለእኛ ትምህርት ሆኗል።

***iii)*** *በሽታ በራሳችን እንዳንመካ ያደርገን ዘንድ ሊመጣብን ይችላል*

ይህንን ደግሞ የምንረዳው ከጳውሎስ ሕይወት ነው።

***2ኛ ቆሮንቶስ 12 (አዲሱ መ.ት)***

*7 ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፣*

*እርሱም የሚያሠቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ።*

*8 ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤*

*9 እርሱ ግን፣ “ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና” አለኝ።*

*ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ።*

ይህ ክፍል ማለትም **2**ቆሮ **12** ስለ መመካት የተሰጠ ትምህርት ነው። ሲጀምርም መመካት ጥቅም ባይኖረውም፣ መመካት ካስፈለገ ግን የምመካበት ነገር ከጌታ የተቀበልኩት ራዕይና፣ መገለጥ ነው ብሎ ይጀምራል። በዚህ ምንባብ ጳውሎስ ምን አይነት ራዕይ እንደ ተቀበለ አይናገርም፤ በሰው አንደበት

ሊገለጥ የማይችል ሰውም እንዲናገረው ያልተፈቀደለት ነገር ሰምቷል። ይህ ድንቅ ነገር ምን እንደሆነ ባይነግረንም ወረድ ብሎ ***"ስለ ራሴ ግን ከደካማነቴ በቀር የምምካበት የለኝም"*** ይላል። ጳውሎስ ይህንን ራዕይ እና መገለጥ ከሰማ በኋላ እንዳይታበይ ***(And least I should be exalted above measure through the aboundance of the revelation [kjv])*** ከእግዚአብሔር የሚያሰቃየው የሰይጣን መልዕክተኛ ተሰጠኝ ይላል። ይህ ምናልባትም ብዙዎች የነገረ መለኮት ሊህቃን እንደሚያምኑት እኔም እንደማሰብው ምናልባት በገላቲያ የሚናገረው በሽታ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በገላቲያ እጅግ ግልጽ በሚመስል መንፈስ እንዲህ ብሏል፡-

*<u>ገላትያ **4** (አዲሱ መ.ት)</u>*

*13 እንደምታውቁት በመጀመሪያ ለእናንተ ወንጌልን የሰበክሁት፣ በሕመም ምክንያት ነበር።*

*14 ሕመሜ ለእናንተ ፈተና ሆኖባችሁም እንኳ፣ **አልሰለቻችሁኝም፤** ወይም*

***አልተጸየፋችሁኝም፤** ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ፣*

*እንዲያውም እንደ ራሱ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አድርጋችሁ ተቀበላችሁኝ።*

ስለዚህ ይህ በቆሮንቶስ ላይ እያለ ያለው ሊያሰለች የሚችል እና አስጸያፊ አይነት በሽታ ነው። ምናልባት ይህንን እያለ እንዳለ አስበን ብናነብ የተሻለ ሚሆን ይመስለኛል። ይህንን ጌታ እንዲያነሳለት ጸልዮም ነበር የጌታ ምላሽ ***"ኃይሌ ፍጹም ሚሆነው ባንተ ድካም ነው"*** በማለት መለሰለት። ስለዚህ በሽታ በሕይወታችን አንዳንድ ጊዜ ትዕቢተኞች በምንሆን ጊዜ ትሁታን ሊያደርገን እና ሰው መሆናችንን ሊያሳየን ሊከሰት ይችላል።

***iv)** በሽታ ተፈጥሯዊ መንገዶችን ተከትሎ ሊመጣ ይችላል*

ይህ ጢሞቲዮስ ላይ የተከሰተው ነው። ጢሞቲዮስ ደጋግሞ የሚነሳበት የሆድ ሕመም ነበረበት ለዚህም በዘመኑ ይደረግ የነበረውን ባህላዊ ሕምክና ይጠቀም ዘንድ ያዘዋል፡-

***1ኛ ጢሞቴዎስ 5፥23 (አዲሱ መ.ት)***

*“ለሆድህና ደጋግሞ ለሚነሣብህ ሕመም፣ ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት*

*እንጂ ከእንግዲህ ውሃ ብቻ አትጠጣ።”*

ማንም ሰው እጁን ሳይታጠብ ምግብ ቢበላ በአይናችን የማናያቸው ብዙ በሽታ አምጪ ተዋሲያን ወደ ውስጣችን በመግባት በሽታን ሊከስቱ ይችላሉ። ክርስቲያ ስለሆን ይህ ተፈጥሯዊ እውነት ሊካድ አይችልም።

በአጠቃላይ የጳውሎስ ምክር ከቃል እምነት መምህራን ምክር ጋር እንዴት እንደሚቃረን ላሳያችሁና ልጨርስ፡፡

***1ኛ ጢሞቴዎስ 6 (አዲሱ መ.ት)***

*6 ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን ነገር ከመርካት ጋር ትልቅ ትርፍ ነው።*

*7 ምክንያቱም ወደ ዓለም ያመጣነው ምንም ነገር የለም፤ ምንም ነገር ይዘን መሄድም አንችልም።*

*8 ነገር ግን ምግብና ልብስ ካለን፣ ያ ይበቃናል።*

*9 ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ፣ እንዲሁም ሰዎችን ወደ*

*መፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ።*

*10 ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ አንዳንዶች ባለጠጋ*

*ለመሆን ካላቸው ጕጕት የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤*

*ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል።*

**...**

*17 በዚህ ዓለም ባለጠጎች የሆኑት እንዳይታበዩ፣ ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር*

*አትረፍርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር እንጂ አስተማማኝነት*

*በሌለው በሀብት ላይ ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።*

*18 መልካም እንዲሠሩ፣ ቸሮችና ለማካፈል ፈቃደኞች የሆኑ እንዲሆኑ እዘዛቸው።*

*19 በዚህ ዐይነት እውነተኛ የሆነውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ፣*

*ለሚመጣው ዘመን ጽኑ መሠረት የሚሆን ሀብት ለራሳቸው ያከማቻሉ።*

ክርስቲያን አይታመም፣ ሊደኸይ አይችልም የሚለውን ዳሳሰዬን እዚህ ጋር አበቃሁ፤ በቀጣይ ዳሰሳዬ እስክመለስ ቸር ቆዩኝ**!!**

## ዋቢ መጽሐፍት


1. Chrstianity in Chrisis, HANK HANEGRAAFF (HARVEST HOUSE PUBLISHER 1973
2. የክርስትና ትምህርቶች እና የእምነት መግለጫዎች ፣ ጥር 2007 የሉተራዊያን የእምነት መግለጫ መጽሐፍ
3. The westmiister confession of faith ቄስ ኃይሉ መኮንን “እምነታችን” ብሎ እንደ ተረጎመው (ኦርቶዶክስ ፕርስቤቴሪያን ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ ትምህርት ሥነ ጽሁፍ አገልግሎት)
4. The westminister Short Cathecism ቄስ ኃይሉ መኮንን “በጥያቄ እና መልስ መልክ የዘተጋጀ ትምህርት ብሎ እንደተረጎመው ተረጎመው (ኦርቶዶክስ ፕርስቤቴሪያን ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ ትምህርት ሥነ ጽሁፍ አገልግሎት)
5. The Reformed Faith_ An Exposition, Robert Shaw
6. Systematic Theology, Vicent Chung
7. Systematic Theology, By Rev. James Petigru Boyce, D. D., LL. D., Joseph-Emerson-Brown Professor of Systematic Theology

The Southern Baptist Theological Seminary
First published in 1887

8. Summary of Chrstian Doctrine, Louis Berkhof